# ምዕራፍ ሀያ አንድ

## የገማ እሣ

ጎንደር በጣልያኖች መያዙ ለራስ እምሩም ሆነ ለደጃዝማች ትልቅ ውድቀት ነበር። ጠላት ጠቅላላውን የሰሜን ድንበር ስለሚቆጣጠር ወደ ሱዳን የሚወስደው መንገድ ተዘግቷል። ራስ እምሩም ወደ ጎጃም የመመለሻ መንገዳቸው የተዘጋ መሆኑን አወቁ ስለዚህ የራሳቸውን ግዛት እንኳን ለመከላከል ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም።

ከብዙ ቀናቶች በፊት ራስ እምሩ ከንጉሡ የተላከ ደብዳቤ ደርሷቸው ነበር። በደብደቤውም ከወታደሮችና ከገበሬዎች ጋራ የተባበረ ግንባር ፈጥረው የጠላትን ግስግሳ ለመግታት እንዲሞክሩ ያን ማድረግ የሚቻል ካልሆነ ደግሞ እራሳቸው ራስ እምሩና ደጃዝማች እያሌው ከንጉሡ ጋር እንዲገናኙና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰፋ በሌለው ጦርነት ለሀገራቸው እንዲሞቱ ጥሪ ነበር። መልሳቸውን በስልክ እንዲያስታውቋቸው ንጉሡ ጠይቀው ነበር።

ንጉሡ ባሉበት ግንባር በሰሜን ምሥራቅ በኩል ስላሉት ሁኔታዎች ምንም ፍንጭ ሳይኖረን ነበር የከረምነው። ይህ ደብዳቤ ብዙ ነገር ነው ያስረዳን። እያንዳንዱን መስመር በፅሞና ላነበበው ሰው ደብዳቤው ንጉሡ ጦርነቱ ያለቀለት እንደሆነ አድርገው እንዳሰቡ ያስረዳል። የደብዳቤው መጨረሻ ራሱ ንጉሡ ጥርጣሬና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንዳላቸውም ያስረዳል። የመጀመሪያና የመጨረሻ የሆነው የንጉሡ ተስፋ ሞቷል።

ከዳባት እስከ ይፋግ(ጣና ሀይቅ አጠገብ ያለ ከተማ) ድረስ የነበረው የቴሌፎን መስመር ጠቅላላ በአካባቢው ሰው ወድሟል። ስለዚህ አዲስ አበባ የሚሆነውን ነገር ለማወቅና በየግንባሩ ያለውን ሁኔታ ለመረዳት ከፈለግን በተቻለ ፍጥነት ወደ ይፋግ ከተማ መሄድ ነበረብን። በደንቀዝ ከተማ ካደረግነው የሀያ ሰአታት እረፈት በኋላ ልክ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቀን የመጨረሻ ጦርነት ባደረግንበት በወሩ መንገድ ጀመርን። የመከራ ጉዟችንም ቀጠልን። አሁንም አንደገና ቅዱስ ጊዮርጊስ ለኛ እንዳልታደገን ለማየት በቃን።



ከከተማው ስንወጣ ከቀኑ አስር ሰአት ነበር ሰማዩን ከባድ ጥቁር ደመና ጋርዶት ነበር። ፈጠነ ተሸሎት በእግሩ መራመድ ይችላል። እኔም ከሶስት ሳምንት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅሎ ላይ በመውጣቴ ደስ ብሎኛል። የጉዟችን የመጨረሻዎቹ ቀናት በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። እርቃኔን ለመሸፈን ስል የዝናብ ልብሴን በየቀኑ መልበስ ነበረብኝ። ሱሪዎቼ ተበጣጥሰው የተንጠለጠሉ ነበሩ። መከራ ቻይ የሆነውን ጫማዬን ለመቆጠብ ሥራመድ በጥንቃቄ ነበር።

መንገድ ከጀመርን አንድ ሰአትም አልሞላም ነበር ድንገት የዝናብ ማዕበል ጀመረ። በህይወቴ እንደዚህ አይነት አይቼም አላውቅም ወደፊትም እንደማላይ ተስፋ አደርጋለሁ። ልክ የማታ ያህል ጨለመ። ቁጥር የሌለው የመብረቅ ብዛት በአጠገባችን መሬት ከሚያንቀጠቅጥ ነጎድጓድ ጋር ይወርዳል። እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ማዕበልም መንፈስ ጀመረ። ፊታችን ሲመታን የነበረው ዝናብ ወደ በረዶ ተቀየረ ያለማቋረጥ ከሁለት ሰአታት በላይ ወረደ።

እንስሶቹ ጭራቸውን ወደ ነፋሱ አዙረው የሚንቀሳቀሱ አልሆኑም። በዚህ ሁኔታ በሜዳ ላይ ያለምንም መጠለያ በግራና በቀኛችን ጎርፍ እየወረደ መቆየት ነበረብን። ከቆምንበት ቦታ በረዶና ውሀ እስከጉልበታችን ድረስ ውጦን በብርድ እየተንቀጠቀጥን ነበር። "ቅዱስ ጊዮርጊስ! ምን በድለን ነው እንደዚህ የፈረድከብን" የሚሉ ንግግሮችም ይሰሙ ነበር ያም ሆኖ ትግሰት ያጠረው ማማረር አልነበረም። እልፎ አልፎ በረዥም መተንፈስ ብቻ ነው። ሰዎቹ ይህንንም ቢሆን እንደታዛዥ ልጅ ነው የተቀበሉት።

ቀጥሎም በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሁልጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ጤነኛ ያልሆነ የመፅናናት ስሜት መታየት ተጀመረ። ከልክ በላይ የሆነ እንደስካርም የሚመስል ሁኔታ ነው። ግን አንድ ሰው ከመጠን ወይም ከአቅም በላይ በሆነ የአእምሮ ጭንቀት ሲወጠር ለማረሳሳትና ለማሳለፍ ይረዳል። አንድ የጅል ቀልድም ተጀመረ። ቀልዱም በአቶ ማሞ ቤተሰ፣ በኢትዮጵያውያን ፓይለቶች፣ በጣልያን ምርኮኞችና በኔ በቀረው ድሬሰር በፈጠነ (ምክንያቱም ሌሎቹ ሁለቱ ስለጠፉ) መሀከል ነበር። ሁሉም በአንድ ጊዜ ይናገራሉ፤ ለመቀለድም ይሞክራሉ፤ እንደገናም በሆነው ባልሆነውም ከልባቸው ከት ብለው ይስቃሉ። የጅል አይነት ቀልድም ነበረ። አንድ ሰው አድጦት ሲወድቅ፤ ወይ ደግሞ አህያ ጭንቅላቱን ከዝናብ ለማስጣል ከሌላው አህያ ሆድ ስር ሲደብቅ፤ ወይ ደግሞ በቅሎ በብርድ እየተንቀጠቀጠ እየር

ሲያመልጠው ነበሩ:: እንደዚህ አይነት ነገሮች ሳቅ ያስጀምራሉ ወዲያውኑ ሁሉም የተሰበሰበው ሰው እንደተለከፈ ሰው መሳቅ ይጀምራል::

ወኔያችም ተመለሰልንና ያ ሁሉ መአት እየወረደብን በጉልበት እንስሶችን ወደፊት ገፋናቸው:: ሸባ እንደሆነ ሰው እዚህ መቆየቱ ምን ይጠቅማል? እንደምንም ታግለን ወደ ታች ወደ ረባዳው መሬት መውረድ አለብን ቢያንስ ቢያንስ ለአሳት የሚሆን እንጨት ይኖራል::

እየተገፋፋንም እየተሻሸንም ነበር:: ሰዎች እየተደናቀፉ ጭቃ በጭቃ ሆነው ውሀ በሞላው ጉድጓድ ውስጥ ይወድቁ ነበር:: ምን ይመጣል? በነዚህ ነገሮች መሳቅ ብቻ ነበር::

በሌላ በኩል ግን በጣም ደካማ የሆኑ ይህን ለመቋቋም አቅም የሌላቸው ሰዎች ነበሩ እነሱም መረዳት ነበረባቸው:: ከነዚህ አንዷ ትንሿ አፀደ ነበረች በሚያሰገርም ጥንካሬ በረዶውን ተቀበለችው:: ባዶ በነበረው በኔ በቅሎ ላይም እሳፈርኳት ነገር ግን በጣም ደከማ ስለነበር እንቅልፍ ወሰዷት ጭቃው ላይ በጭንቅላቷ ወደቀች:: ከዚያ በኋላ  እኔና እንደኛው ፓይለት በየተራ እንሸከማት ነበር::

ከምሽቱ ሶስት ሰአት ብሰብሰ እንዳልን ሰውነታችን በሙሉ በጭቃ እሰከ ጆሮአችን ድረሰ ተለቅልቆ ግራኝ በር ደረሰን:: ወዲያውኑ ለእሳት የሚሆን እንጨት ለመልቀም እሽቅድድም ተጀመረ::

“እባባ ቶሎ ናልኝ” ተመልሳ ነቃ ያለችው አፀደ ነበረች እኔን ስትጠራ የሰማሁት::

እየሮጥኩ ሰደርሰ ከእቅሟ በላይ እሰር እጥፍ የሚሆን ግንድ ላይ ተጋድማ ባለ ጉልበቷ ግዙፍ ከሆነ አገልጋይ ትከላከላለች::

“ግንዱ የኔ ነው! መጀመሪያ ያየሁት እኔ ነኝ” እያለች በመጮህ እንደ እነር እየዘለለች የግዙፉን አገልጋይ እግር ትደበድብና ትናከሰ ነበር::


ሶሰት ቦታ በሚነድ ትልልቅ እሳት ዙሪያ ተቀመጠን ልብሳችንም ወዲያው ደረቀ ቡናም እፈላን ከደንቀዝ ያመጣነውን እንጀራና ወጥም በላን:: እሁን የነበረን ሰሜት ቀዝቀዝ ማለት ጀመረ ደግነቱ ደከሞን ሰለነበር የማገገሚያው መልእከ እንቅልፍ በትክከለኛው ጊዜ ደረሰልን::

ማዕበሉ ከነበረዶው በጣም ሀይለኛ ቢሆንም ለኛ ጠቀሜታ ነበረው:: ነግቶ በጣም ወላኝ በሆነና በቀላሉ በማይታለፈው በግራኝ በር ማለፊያ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያን የወረረው ግራኝ መሀመድን ያስቆሙበትና የተገደለበት ቦታ ለናልፍ ያየነው ነገር ነበር:: ማለፊያው በጉድባና በግንብ የተዘጋጁ መተኮሻ



ምሽጎች ተሰርተውበታል:: ለካሰ የእካባቢው ገበሬዎች እኛን ላለማሳለፍ ቆርጠው ተዘጋጅተው ነበር:: ነገር ግን ማታውኑ ማዕበሉ በመምጣቱ ዕቅዳቸውን አፈረሰባቸው:: እዛ ቦታ ላይ ከመጠን በላይ በረዶ የወረደ ይመሰላል ምከንያቱም ግዙፍ የሆኑ የበረዶ ክምሮች በየቦታው እናይ ነበር፡

በማለፊያው ደግሞ ግራኝ በፅኑ ሲቆሰል በንዴት በጎራዴው መትቶ ሊቆርጠው ነበረ የተባለውን የተጠማዘዘ የወይራ ዛፍ እየን:: ይህ ዛፍ ራሱ ይሁን እርግጠኛ እልነበርንም ግን ይመሰላል ምክንያቱም ዛፉ በዘጠና ዲግሪ የተጣመመበት ቦታ ላይ የጠባሳ ምልክት ይታይ ነበር።



አሁንም በጎንደር ግራኝ በር በሚባል ቦታ (ፀሐፊው እለፍንበት ባሉበት) የሚገኝ ግራኝ መሀመድ ሲቆስል ተበሣጭቶ በጎራዴ የከተከተው የሚባለው የወይራ ዛፍ በተለያየ አቅጣጫ የተነሳ ፎቶ (ከላይና ከስር) (2007ዓ.ም.)

---

*ግራኝ አህመድ በዚህ ሰፍራ ኢድፍጦ በተኮሰ ሰው ጥይት የተመታ ሲሆን ተኳሹ ደግሞ የፖርቱጋል ወታደሮች አዛዥ የነበረው የከርሰቶፎር ደጋማ የግል ዘብ ነው:: ክርሰቶፎር ደጋማ የታዋቂው አሳሽ የቫሰኮ ደጋማ ወንድም ነው ወደ ኢትዮጵያ ለእርዳታ አራት መቶ ወታደሮች ይዞ መምጣቱ ይታወቃል:: ክርሰቶፎር ደጋማ ተማርኮ በግራኝ እጅ ሰለተገደለ ተኳሹ የአሊቃውን ደም ተበቀለ ተብሏል:: ግራኝ አህመድ በዚህ ቦታ ሲሞት ተከታዮቹ ሸሽተው ወደ ሐረር በመመለሰ በከተማው ግንብ እንደሠሩ ተዘግቧል:: ከተለያዩ መረጃዎች የተሰበሰበ:: (ተከለፃድቅ መኩሪያ ፣ ሪቻርድ ፓንክረሰት፣ ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮፒካ)*



በቀን ብዛት ያላቸው አውሮፕላኖች ይመጡብን ነበር ግን ምንም አይነት የመተናኮል ሁኔታ አላሳዩም። በጣም ዝቅ ብለው በላያችን ላይ ደጋግመው ይበሩ ነበር ምንም ነገር አልጣሉብንም። የኛ ሰዎችም ቢሆኑ ወደ አውሮፕላኖቹ የመተኮስ ፍላጎት አልነበራቸውም።

ማታውን በእጠገቡ የጥንት ቤተመንግስት ፍርሥራሽ በሚታይበት በአሰደሳቹ የአርኖጋርኖ ወንዝ ዳርቻ አሳለፍን። በሚቀጥለው ቀን ተጉዘን በመጋቢት ሀያ ሰድሰት እኩለ ቀን ላይ ይፋግ ከተማ ገባን።
የጦር አዛገ‌ሮቹ ወዲያውኑ ከአዲስ አበባ ጋራ ግንኙነት አደረጉ። የቴሌፎን ሠራተኛው የጎንደሩ መሰመር ተቋርጧል አለ በኋላ ሰናጣራ ግን ውሸት ነበር። ሰውየው ከጣልያኖች ጋራ ሲገናኝ ነበር አሁንም ይገናኛል።

ከሁለት ሰአታት ደወልና ጩኸት "ሀሎ!" በኋላ ከአዲስ አበባ ጋራ ግንኙነት ተጀመረ። ግንኙነቱም በመሀል መቀባበያ ጣቢያዎች በደብረታቦር፣ አጋት፣ በሽሎ፣ መቅደላና ወረኢሉ በኩል አደርጎ ነበር።

ራሰ እምሩ የመጀመሪያውን እድል ስለወሰዱ ከሁለት ሰአት በላይ ለሚሆን ጊዜ ማውራት ቀጠሉ ደጃች አያሌው በትግሰት ውጭ ሆነው እየተጠባበቁ ነበር። ከዛም የደጃዝማች ተራ ደረሰና አሳቸውም ተመሳሳይ ረጅም ንግግር



አደረጉ። ከዛ በኋላ ሁለቱም በአየጃቸው መገናኛውን ይዘው ተቀመጡና ከአዲስ አበባ ጋራ ከአንድ ሰአት በላይ ተነጋገሩ።

በመሀሉ እንደነሱ ብዙም ጭንቀት የሌለብን እኛ ደግሞ ጊዜያችን ደሰ በሚል ሁኔታ ለማሳለፍ አሰበናል። መልክተኛ ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ ወደኛ ሲመጣ በከተማው ውሰጥ ባለ አንድ የመኖርያ ቤት ደምበኛ አራት ግብዣ አዘጋጅተን እየተደሰትን ነበር። መልከቱም አዛገ‌ሮቹ ንግግራቸውን ሰለጨረሱ ከከተማው ብዙ ኪሎ ሜትሮች ራቅ ባለ የካምፕ ቦታ እንድንሄድ ነበር።

ለብዙ ሰአታት አዲስ አበባ ካሉ ገዥዎች ጋራ ንግግር ቢያደርጉም ደጃች አያሌው ስለ አቢሲኒያ ምን እንደተደረገና ምን እየሆነ እንደሆነ ያገኙት ዕውቀት የለም። በኦፊሲያል አቴጌይቱ ሀላፊ እንደሆኑ ነው የተነገረው ነገር ግን በርግጥ ሀላፊ የነበሩት የንግድ ሚኒስትሩ አቶ መኮንን እንደሆኑ ነው የተረዳነው።

"እንዲህ ከሆነ ነገሮች በሙሉ መጥፎ ደረጃ ደርሰዋል" አሉ ደጃዝማች የሰሙትን ነገር ሲነግሩኝ። እኔ እንኳን ገብቶኛል ምክንያቱም የተከበሩ ሚኒስትሩን በደንብ አውቃቸው ነበር። በትልቁ ምንም አይነት የሚረባ ነገር የሌላቸውና ከዚህ በፊት ታይቶም ተፈጥሮም የማያውቅ በጣም የገማ አሳ ማለት ነበሩ።

ትንሽ ዘግይቶም የጦር ሚኒስትሩ ልጅ የራስ ካሳ እና የራስ ሰዩም ሠራዊት የተሸነፈ መሆኑ ታወቀ። ሆኖም እንደሚኒሰትሩ አቶ መኮንን አገላለፅ ይህ አደገኛም አልመሰለም ምክንያቱም ንጉሡ ብዛት ያለው ሠራዊት ይዘው ወደ ጦር ግንባር እየሄዱ ሰለሆነ ጣልያኖችን በመጡበት መመለሰ ይችላሉ። እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ሠላም ተመልሶ ይመጣል። በአጋዴን በኩል ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ የግራዚያኒን ሠራዊት ሙሉ በሙሉ ሲደመሰሱት ምንም አልቀራቸውም ነበር። ራሰ እምሩና ደጃች አያሌውን በተመለከተ እርሰ በርሳቸው ከተመካከሩ በኋላ ይበጃል ብለው ያሰቡትን ነገር ሲያደርጉ ነው። እንግዲህ በቆራጥነትና በአገር ወዳድነት ሰለተዋጉ በንጉሣውያን ቤተሰቦች መታመንና መልካም ፈቃድን አግኝተዋል።

በኋላ እንኳን ሰለዚህ ቅጥፈት ሳሰብ በንዴት ብዛት ያጥወለውለኝ ነበር። እንግዲህ ይህን ያደረጉት ቀበሮው አቶ መኮንን ናቸው። ያን ሁሉ ሰአት በሰልክ ንግግር ሲለዋወጡ እነዚህን ሁለት የተከበሩ ሰለ አባት አገራቸው ሁኔታ የተጨነቁ ሰዎችን በውሸት ሲደልሉዋቸው ነው የቆዩት። ራሰ እምሩና

ደጃች አያሌውን፡፡ ምንም አይነት መረጃም የላቸውም እናም ሀይልም አልነበራቸውም ስለዚህ በሙሉ እምነት ከአዲስ አበባ ገዥዎች ባለው ሁኔታና ወደ ፊት ስለሚሆነው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ምክር ጠየቁ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያሉ ነው ሚኒስትር ተብየው አዲስ አበባ ቁጭ ብለው ሰዎቹን ጆሯቸው እስኪሞላ ድርስ ምንም አደጋ የለም እያሉ ሲነግሯቸው የነበር፡፡ ሚኒስትሩ ግን ንጉሡ ሸሽት እንደጀመሩ ያውቁ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ቀን ወደ ጎጃም ለመሄድ ከወሰኑት ከራስ እምሩ ጋራ ተለያዬን፡፡ ለኛ የነበረን እማራጭ ወደ ደብረ ታቦር መሄድ ነው፡፡ ደብረ ታቦር የደጃዝማች አያሌው አማች ደጃዝማች እስፋወሰን ነበሩ አዛዡ፡፡ ከአምስት መቶ ከማይበልጡ ወታደሮች ጋራ በመሆን በመጋቢት ሰላሳ በጠዋቱ ደብረታቦር ገባን፡፡ ከተማው ዙርያው ያምር ነበር፡፡

እኔና ፓይለቶቹ ጓደኞቼ መጀመሪያ ያደረግነው ነገር ቢኖር አውሮፕላን እንዲላክልን ወደ አዲስ አበባ ቴሌግራም ማድረግ ነበር፡፡ መልሱም ከጥቂት ቀናት በኋላ በቴሌግራም ተላከልን፡፡ ከእቴጌዋ ነበር የተላከው፡፡ አውሮፕላን መላክ እንደማይቻል ነው የተገለፀልን፡፡ ለደህንነታችን ሲባል ከደጃዝማች አያሌው ጋራ እንድንቆይ ተነገረን፡፡

ቴሌግራሙን ከላኩ በኋላ ወደ እድቬንቲስት ሚሲዮን ማዕከል ሄድኩኝ በሶስቱ አውሮፓውያን ታላቅ የወዳጅነት አቀባበል ተደረገልኝ፡፡ ሚስተር ፓልም ስዊድናዊ፤ ሚስስ ፓልም ኖርዌይ እና በአንግድነት የመጣው ጀርመናዊው ሚስተር ሄስ ነበሩ፡፡ በደብረታቦር ለአንድ ሳምንት በቆየሁበት ጊዜ በሚስተርና ሚስስ ፓልም ቤት ነበር በአንግድነት ያረፍኩት ሚስትር ሄስም አዛው ቤት ነው ያለው፡፡ ገላ ለመታጠብና ፂሜን ለመላጨትም እድል አገኘሁ፡፡ የራሴ ፀጉር ትከሻዬ ላይ ይደርስ ነበር፡፡ ሄስ ፀጉሬን ቆረጠልኝ፡፡ ሚስትር ፓልም ደግሞ ሱሪ ሰጠኝ፡፡

---

*አጼ ሀይለ ሥላሤ በስደት በነበሩበት ጊዜ ራስ እምሩ በሀገር ውስጥ የንጉሡ ተወካይ ወይም እንደራሴ ነበሩ፡፡ በዚህ ምክንያት ይኖሩበት የነበረው ከተማ ጎሬ ለተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነበረ፡፡ ከከባድና ከፍተኛ ውጊያዎች በሁዋላ ራስ እምሩ በታሕሣሥ ዘጠኝ ለጣልያኖች እጃቸውን ሠጥተዋል፡፡ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ወደ ግራዚያኒ ተልከው ነበር ቀጥሎም ወደ ሞሶሎኒ ወደ ሮማ ከተላኩ በሁዋላ ፖንዛ በሚባል ደሴት የቁም እስር ሆነው ነበር፡፡ የሚገርመው ነገር ከሰባት አመታት በሁዋላ ሞሶሎኒ ራሱ በዚህ ቦታ ታስሮ ነበር፡፡*
*Haile Selassie's War by Anthony Mockler*
*በተመሳሳይ ሁኔታም ደጃዝማች አያሌው ጣሊያን ውስጥ እሲናራ የሚባል ደሴት በቁም እስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡ ከተመለሱ በሁዋላም ለሁለተኛ ጊዜ ተዋግተው እንደገና እንደተማረኩ ተዘግቧል፡፡*
*(ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮፒካ)(ጎንደሬ ቢጋሻው በገሪማ ታፈረ)*



ለአምስት ወራት በየጫካው ከርታታ ኑሮ ስኖር ከርሜ አሁን ግን ንፁህና ደስ የሚል በስዊድን ባህል የተዘጋጀ ጠረጴዛ አጠገብ ስቀመጥ የተሰማኝ ስሜት መግለጫ የለውም፡፡ የውነት አልጋ ላይ ንፁህና ጥሩ ሽታ ያለው ነጭ አንሶላ ውስጥ ገብቼ መተኛት ደግሞ የነበረኝን ስሜት ከፍ ነው ያደረገው፡፡ በአራት ማዕዘን ግድግዳ ያለው ቤት ውስጥ መተኛት መቻልስ የሚሰጠው የደህንነት ስሜትስ! ምስጋናዬ ለእነዚህ ለረዱኝና ለተንከባከቡኝ ጓደኞች ልክ የለውም ወደፊትም ቢሆን ሳመሰግናቸው እኖራለሁ፡፡

የሚያምረው የሚሲዮን ማዕከል ከከተማው ጠርዝ ነው የሚገኘው፡፡ የጠቅላላው የሚሲዮኑ ቅጥር ግቢ ወደ 35 ሄክታር ይሆናል ዙሪያውንም በአጋም ተክል ታጥሮአል፡፡ ግቢው ውስጥ ደግሞ በጣም ጥሩ ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ ሰዎች መያዝ የሚችል ሆስፒታል፣ የአፐሬሽን ክፍልና ክሊኒክ ፤ ሶስት የመኖርያ ቤቶች፤ ትምህርት ቤትና ቤተክርስቲያን አሉበት፡፡ በደንብ በእንክብካቤ የተያዘ የአትክልት ቦታና ብዙ ሺ ለአይን የሚያስደስቱ የባህር ዛፎች ያሉበት መናፈሻ ቦታም አለው፡፡ ሁሉም ነገር በደንብ በሥነሥርአት ነው፡፡ እኔም ምቾት አልጎደለኝም፡፡ ከራሳቸው ጄኔሬተር የኤሌክትሪክ መብራትም ነበር፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ስለተዘጋ ትምህርት ቤቱ በዚያን ጊዜ ለአቢሲኒያ ባንክ የደብረታቦር ቅርንጫፍ በኪራይ ተሰጥቶአል፡፡ ባንኩም ወስጥ የሚሰሩ አሜሪካ የተማሩ ሁለት ወጣት አቢሲኒያውያን ጋራ ተዋወቅሁ፡፡

ፓልም ቤት ውስጥ የተሠራ የሚገርም ሬዲዮ ማዳመጫ ስለነበረው በውጭው አለም የሚደረገውን ነገር መከታተል እንችል ነበር፡፡ ያው ፀጉር የሚያቆም ዜና ተራ በተራ ቢያሰማንም ለኔ ደግሞ ትልቅ ዜና የሆነው አቢሲኒያ ውስጥ የሚደረገው ነገር ነበር ፡፡

ጠቅላላው የሰሜን ግንባር እልቆለታል ንጉሡም እየሸሹ ነበር፡፡ የት እንዳሉ ግን ማንም አያውቅም፡፡

የአዘቦና የወሎ አሮሞዎች ድሮ የደረሰባቸውን በደል ለመበቀል ከግንባር የሚመለሰውን ጦር ይዘርፉትና ይወጉት ነበር፡፡

ራስ ሙሉጌታና ልጃቸው ተገድለዋል

ጣልያኖቹ ጉዟቸውን ወደ ደሴ እየቀጠሉ ነበር፡፡ አረንጓዴ ነጭና ቀይ ቀለም ያለው የጣልያኖች ባንዴራም በጣና ሀይቅ ዳርቻ ለሀያ አራት ሰአታት ይወለበለብ ነበር፡፡ በኦጋዴን ግንባር አቢሲኒያውያኑ መከተው እንደያዙ ነው ነገር ግን የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ መስመሩ መሰበሩ አይቀርም፡፡

አቅም የሰሹ ሊግ እፍ ኔሽንስ ስብሰባ በመጥራትና እስተያዩት በመደርደር ጊዜ እያጠፉ ነው፡፡

የንጉሡ ሀይለኛ ተናጋሪ የነጭ አማካሪዎች በሙሉ አገሩን ለመልቀቅ የተገኘውን አጋጣሚ እየተጠቀሙ ነው ምክንያቱም ሁኔታው ደካማና አደገኛ ነው ብለው አሰበዋል፡፡

በግልፅ አጠቃላይ የሆነ ድምዳሜ እለ ነገር ግን ገና በጦርነት ያልተሸነፈው የአሊጋ ወራሹ ጦር በቦታው እያለ ጠላት እንዴት ብሎ ነው ደሴ ድረስ የዘለቀው? እንዲህ ብለን ነበር እኛም እሰበን የነበረው፡፡

ፋሲካን በደብረታቦር ከአከበርን በኋላ ወዲያውኑ በጋይንትና በመቅደላ አድርገን ወደ ደሴ መጓዝ ነበረብን፡፡

በየቀኑ የሚሸሹ የራስ ካሳ ሰዎች ይመጡ ነበር፡፡ እነዚህን የተጎዱ ወታደሮች ማየት በጣም ያሳዝን ነበር፡፡ አቅም ያነሳቸው ዕራፊ የለበሱ በተቅማጥና በፈንጣጣ የደከሙ ነበሩ፡፡ በየቀኑ በእስሮች ቤት የሚቆጠሩት እየሞቱ ነበር የቤተከርስቲያን ቅጥርም በቂና ሰፊ ስላልነበረ በየሜዳው ነበር የሚቀበሩት፡፡

አንድ ቀን አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ከብዙ መቶ ወታደሮች ጋራ ሸሽቶ መጣ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ ሊሄድ ነው፡፡ የባንክ ሠራተኞቹ ፓይለቶቹ እና እኔም ልንከተለው ወሰንና ተዘጋጀን፡፡ ደጃች አያሌው ግን እኔን እንዳልሄድ ከለከሉኝ፡፡ አያሌው ሁኔታው በጣም አደገኛ ነው ያሰቡት በታም አይደርሱም እሉ፡፡ ለመንኩ ፀለይኩ ቢከለከሉኝም እሄዳለሁ ብዬ አስፈራራሁ፡፡ "የራሴ አሰቃ ራሴ አይደለሁም እንዴ?" አይሆንም!፡፡ እሄዳለሁ ብዬ ከሞከርኩ እንደሚያስሩኝ ነገሩኝ ምክንያቱም በመንገድ ላይ እንድገደል አልፈለጉም፡፡

ስለዚህ ሌሎቹ ጥለውኝ ሄዱ፡፡ በመቅረቴ ተፀፅቼ አላውቅም፡፡ በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁሉም ተገደሉ፡፡



# ምዕራፍ ሀያ ሁለት

## መከበብ

በበጌምድር በራስ ካሳና በልጆቻቸው በአስፋወሰንና በወንድ ወሰን ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበር፡፡ ምክንያቱም በራሰ ወዳድነት የመሠረቱት የግብር ሥርአት ገበሬውን የሚበዘብዝ ነበር፡፡

እያንዳንዱ ገበሬ ካመረተው ሰብል አንድ አሥረኛውን ዋጋ
ስእያንዳንዱ በሬ ሁለት ማር ተሬዛ
ለበግ አንድ አሰረኛ
አንድ ማር ትሪዛ በጭስ (በጎጆ ማስት ነው)
ከዶሮ አንድ አሥረኛውን
ለሠራዊቱ የሚሆን አራት ማር ትሬዛ
ሁስት ማር ትሬዛ ለፍርድ ቤት
ገበያ ላይ ስተሸጡ ማንኛውም እቃዎች አንድ አስረኛውን ዋጋ
በተጨማሪም ደግሞ ለአገረ ገዥው በድምሩ የሰላሳ ቀን የጉልበት ሥራም ነበረበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከጠቅላላ ገቢ አንድ አስረኛውን ለቤተከርስቲያን ብዙ ጊዜ ደግሞ ተጨማሪ ግብር ስማዕከላዊ መንግሰት ይሰበሰብ ነበር፡፡ በድምሩ የበጌምድር ገበሬ ከአመት ገቢው ከሀምሳ እስከ ስልሳ በመቶ (ፐርሰንት) ድረስ ይገብር ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ እንግዲህ ያሁኑ ገዥ አስፋወሰን ደብረታቦር ሳለመቆየት ቢወስኑ እንግዳ ነገር አይሆንም፡፡ ከኛ ጋራ በመሆን አዲስ አበባ ስመሄድ ወስነዋል፡፡ ያገሩ ሰዎች በምስጢር ወደ ጣልያኖች ወደ ጎንደር ተወካይ ልከው ጣልያኖቹን የተቀበሉ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደሞከሩ አሰፋወሰን ያወቃሉ፡፡ ከሌሎች ከተሞች ተለይቶ ደብረ ታቦር በቦምብ ያልተደበደበት ምክንያትም ይህ የምስጢር መልክት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በሚያዝያ ስድስት በጠዋቱ የኔ አለቃ ደጃች አያሌው ከአማቻቸው ጋር በመሆን ከተማውን ጥለው በመውጣት በምሥራቅ በኩል የአንድ ማይል ርቀት ላይ ካምፕ መሰረቱ:: እኔ ራሴ ምሽት እስከሚሆን ዘገየሁኝ ምክንያቱም ከጓደኞቼ ከሚሲዮናውያኑ ጋር እስከተቻለ ድረስ አብሬ መቆየት ፈልጌአለሁ:: የነሱን ምክር መቀበል ግን አልፈለግሁም:: ምክራቸውም ጣልያኖቹ እስከሚመጡ ድረስ ከነሱ ጋር ሆኜ እንድጠብቅ ነበር:: የአቢሲኒያ መንግስት ሠራተኛ ስለሆንኩ ራሴን አሳልፌ ለመስጠት አልወሰንኩም::

ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ አይነት ነገር ማድረግ ደጃዝማችን መክዳት ነው ብዬ አምናለሁ:: ምንም አንኳን ወደፊት ምንም የምረዳቸው ነገር ባይኖር በክፉ ጊዜ ከጎናቸው መቆም የኔ ሀላፊነት ነው ብዬ አስቤያለሁ::

ማታው በችኮላ ነው የደረሰው ስለዚህ ጓደኞቼን ትቼ መሄድ ነበረብኝ:: ልቤ እየተንተተ በቅሎዬ ላይ ተሳፍርኩና ጀርባየን ለአስደሳቹ የሚሲዮን ጣቢያ ሰጠሁኝ:: ለአጭር ጊዜ በሚሲዮኑ ጣቢያ ባሳለፍኩበት ጊዜ የለመድኩትን አኗኗር ጭልፍታ አይቼ ነበር አሁን ግን እንደገና እየተዘጋብኝ ነው:: እንደገና ደረቁ መሬት መኝታዬ ሊሆን ነው:: እንደገና አምስት ጣቶቼን እንደ ሹካ ልጠቀም ነው:: እንደገናም ከቅማል ጋራ ልገናኝ ነው እንግዲህ ይህን መድረሻው ያልታወቀ ያልተቋረጠ የመከራ መንገድ ልቀጥል ነው::

ለአንደ አፍታም ቢሆን አይታው ብሩህ ነበር:: የማስታውሰው ትዝታ አግኝቻለሁ:: ወዳጅነት የሚያሳዩ ሰዎች ትዝታ፤ በሰላም ያሳለፍኳቸው ሰአቶች፤ ሰላማዊ የነበሩ የማንበቢያ ቀኖች፤ ከሰዎች ጋራ ያደረግሁት ተህድሶ የሚሠጥ ንግግር:: ይህ ትዝታ እንግዲህ የሚመጣውን አዲስ ማዕበል ለማሳለፍ ይረዳኛል::

ግማሽ መንገድ በጀርባዬ ትቼ ነበር ጨለማው መስፈን ሲጀመር:: በአካባቢያችንና በተለያዩ አቅጣጫ የተኩስ ድምፅ መስማት ጀመርኩ:: የውሻ ጥርስ የሚባል ማለፊያ ቦታ ላይ ነበር:: ከፍታው ላይ ባሉ ሰዎች አንድንቆም ታዘዝን::

በቅሎውን ሲመራ ከነበረው ወታደር ጋራ በመሆን ከኮርቻ ወርጄ ጥይቶች በጎናችን እያፏጩ በታቻለ ፍጥነት መሮጥ ጀመርን:: ትንሽ መቶ ሜትሮች ወደፊት እንደሮጥን ወንዝ አጠገብ ስንደርስ ደጃች አያሌው የሰጡኝን አውቶማቲክ መሳሪያ ጠመድን::

የተኩሰ ልውውጡ ለደቂቃዎች ቀጠለ ቆይቶም የተፋጠጡት ከአውቶማቲክ መሳሪያ ጋራ ስለነበር ወንበዴዎች ተኩሰ በማቆማቸው ደስተኛ



ሳይሆኑ አይቀሩም:: ከዚያ በኋላ መንገዳችን ያለምንም ረብሻ መቀጠል ቻልን::

በሚቀጥለው ቀን በበጌምድር አረንጓዴና ለምለም ነገር ግን ቀዝቀዛና ደጋማ በሆነው ክፍል አቋርጠን መጓዝ ቀጠልን:: በየቦታው ብዛት ያለው የቀንድ ከብት የበግ የፈረስና የበቅሎ መንጋ አየን:: ለመጀመሪያ ጊዜ በአቢሲኒያ በፈረስ የሚያርሱ ገበሬዎች አየሁ ሌላ ጊዜ በበሬ ነው የሚታረሰው::

አመሻሽ ላይ ደጃዝማች አያሌው ከአካባቢው ሰዎች በጣም ቁምነገር ያለው መልክት ይዘናል የሚሉ ተወካዮችን ተቀበሉ:: በዚያን ጊዜም ግልፅ የሆነው ገበሬዎቹ ደጃች አያሌው በመካከላቸው አልፈው ቢሄዱ ችግር እንደሌለባቸው ነው:: ደጃማቹ ችግር ላይ እንደሆኑና ንጉሡን ለመገናኘት እንደሚሄዱ አውቀዋል:: ነገር ግን ደጃማች ከራስ ካሳ ልጅ ከአስፋወሰን ጋር አብረው እንዳይጓዙ ጠየቁ ምክንያቱም የራስ ካሳ ልጅ በመሬታቸው አልፈው እንዲሄዱ አልፈለጉም:: ሲጨቁኗቸው ስለኖሩ የነሱ እንባ ሲፈስ እንደኖረው ሁሉ ደማቸውን ካላዩ እንደማይረኩ ገለፁ::

"በጥያቄያችሁ ባልሰማማስ?" ብለው ጠየቁ ደጃዝማች ምንም አይነት የሰውነት ምልክት ሳያሳዩ

"መልካም፤ ህዝቡ አማራጭ የለውም ስለዚህ አያሌውም ቢሆኑ የበዳዮቹን ዕጣ ይካፈላሉ"

የደጃዝማች ደማቸው ነው የፈላው:: ቀጥሎም

"አስፋወሰን እኔ እስከፈቀድኩ ድረስ አብሮኝ ይሄዳል:: አናጠቃለን ብላችሁ ከደፈራችሁ መላኩ ገብርኤል ይርዳኝ ቤታችሁንና እናንተን አቃጥላችኋለሁ የመትረየሴ ሳት ራት ትሆናላችሁ" አሉ::

ቅዱሰ ገብርኤል የአያሌው ጠባቂ መልአከ ነው:: አያሌው በገብርኤል ከማሉ አለቀለት ማለት ነው ይህንንም ድፍን አቢሲኒያ ያውቀዋል::

ከገበሬዎችም የመጣ ጥቃት አልነበረም:: ከፍታው አራት ሺ ሁለት መቶ ሜትር የሆነው ጉና ተራራ ለንደርስ በብርድ ሰውነታችን ሲረጋ ምንም አልቀረውም:: አስፋወለንም የመረጋጋት ስሜት ተሰማቸው:: አዲስ አበባ ቶሎ ለመድረስ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከኛ ተለይተው ሄዱ:: ከሳቸውም ጋራ

አምስት መቶ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ በተጨማሪም የኛ የጣልያን ምርኮኞችና ሌሎች ሶስት በራስ ካሳ የተማረኩ ወደ ደብረታቦር የተላኩ ጣልያኖችም ነበሩ።

እኛ ደግሞ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ደሴ የሚወስደውን መንገድ ያዝን። መጀመሪያ ደጃች አያሌው የትውልድ ቦታቸውን በጋይንት የሚገኘውን ኤፍራታን ማየት ፈለጉ። እናታቸውንና ወንድማቸውን መጠየቅ ፈልገዋል። ልጃቸው ሳይሰሙ እናትየዋ ከሞቱ መንፈቅ አልፏል።

ጋይንት ስንደርስ የደጃዝማች አድማሱ እንግዶች ነበርን። አድማሱ ከወንድማቸው ከአያሌው ጋራ የሚያመሳስላቸው ነገር የለም። ተጫዋች ናቸው ወፍራምም ነበሩ። አድማሱን በሕይወታቸው በጣም የሚያስደስታቸው ነገር ጥሩ ምግብ ከጨዋታና ከሳቅ ጋር ተበልቶ የሚመች አረፍት ማድረግና ቀኑን ሙሉ መተኛት ነው። ሌላ የተለየ ባህሪ ካላቸው ደግሞ በቆይታ የሚታይ ነገር ነበር።

ለማደሪያ የተሠጠኝ ትልቅ ድንኳን ነበር በጣራው ላይ ትልቅ ቀይ መስቀል ተስሎበታል። አድማሱን ምን ማለት ነው ብዬ ስጠይቅ ቀይ መስቀል ያስቀባሁት ጣልያኖቹ እንዳይደበድቡት ለማታለል ነው በማለት የጮሌ መልስ ሰጡኝ። ይህንን ማታለል የጀመሩት ራስ ካሳ ናቸው እሳቸውን ተከትሎ ጦሩም ቀጥሎበታል። "ስለዚህ" አሉ አድማስ በረዥሙ እየተነፈሱ "ብዙ ሳይቆይ ጣልያኖቹ ማታለል መሆኑን ማወቅ ይጀምራሉ"

በርቀት የመቅደላ ተራራ ይታየናል ወደ ትልቁ የበሽሎ ወንዝ ለመሄድ እየተዘጋጀን እያለን ደሴ በጣልያኖች መያዙን የሚገልፅ ዜና ደረሰን። የማይታመን ነገር ነው የመሰለው ደጃዝማችም እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሁለት ሰዎች ላኩ።

ከአምስት ቀናት በኋላ መልክተኞቹ ተመለሱ የተወራው ነገር እውነት መሆኑንም አረጋገጡ እንዲያውም ብዙ ተጨማሪ ወሬ ይዘው መጡ። ጣልያኖቹ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ወስነው ወደፊት እየገሰገሱ ነው። የያዟቸው መኪናዎች ብዛት ስላላቸው መቁጠርም አስቸጋሪ ነበር።

አሁን ያለን አማራጭ ሁለት ብቻ ነው። ወይ ወደ ምዕራብ በኩል ወደ ጎጃም መሄድ አለዚያም ወደ አዲስ አበባ መቀጠል ነው። ወደ አዲስ አበባ መሄዱ ጥሩ ሀሳብ መሰለ ለማንኛውም ለደህንነት ሲባል ሁለት መልክተኞች ወደ አዲስ አበባ ሄደው ሁኔታውን እንዲያጣሩ ተደረገ።



በዚህ ሁኔታ እያለን ውሎ አድሮ መከበባችን ግልፅ ሆኖ ታወቀ። የስማዳ ገበሬዎች በምዕራብ እና በደቡብ በኩል ተሰባስበዋል። ደፍሮ በመሬታቸው በኩል የሚያልፈውን ማንም ሰው ለመግደል ወስነዋል። አስፋወሰን በብልጠት ሾልከው አምልጠዋል። ገበሬዎችም እንዲህ ያለ ነገር አይደገምም ብለዋል። ሁለቱ የአቢሲኒያ ፓይለቶች የባንኩ ሠራተኞችና አብሮ የነበረው ጦር ለአራት ቀናት እራሳቸውን ተከላክለው ነበር ሆኖም በመጨረሻው ተገድለዋል።

በሚያዝያ ሀያ አንድ ጣልያኖቹ ደብረ ታቦር ከተማ ገብተዋል። ከሳምንት በኋላ ደግሞ ያ የምናውቀው *መሀመድ ኢማም የኤርትራው ገገር የጋስፓሪኒ መልከተኛ ሆኖ መጣ። ሀሳቡ እንግዲህ ይህን የሚያህል ትልቅ ሰው ደብረ ታቦር ድረስ በድካም መምጣቱ ለአያሌው ወዳጅነት ተብሎ ስለሆነ መሀመድ ኢማም አያሌው እጃቸውን እንዲሠጡ ሊያሳምናቸው ይችላል ነው። ደጃዝማች ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳያደረጉ ምክር ተሠጣቸው። ቢያደርጉ የሚጎዱት እሳቸው ናቸው ምክንያቱም የኃይል ሥላሴ መንግሥት የሚባል ነገር የለም።

ጋስፓሪኒ ፊርማው ያለበትና ማህተም በተደረገበት ደብዳቤ አያሌው መልካም አመለካከት ካሳዩ ምንም እንደማይደረጉ ዋስትና ሰጥቷል። የተከበረው የኤርትራው ገገር ለአያሌው የራስ ማዕረግ ከነሙሉ ጥቅሙ እንዲሠጣቸው ከጣልያን መንግስት ሊጠይቅላቸው አስቧል።

ደብዳቤውን ካሳረከበ በኋላ የተከበረው አስታራቂ ማስታወቅ የፈለገው በግሉ በራሱ በወዳጅነት እንደመጣ እንጂ በጣልያን መንግሥት እንዳልተላከ ነው።

መሀመድ ኢማም በመጣ በሁለተኛው ቀን ወደ አዲስ አበባ ተልከው የነበሩት ሁለቱ ፈጣን መልክተኞች ተመለሱ። እንዴት አድርገው የሶስት መቶ ኪሎሜትር ርቀት በሶስት ቀን ተኩል እንደሸፈኑ ለመግለፅ አስቸጋሪ ነው። እንጦጦ ጋራ ላይ ሆነው አዲስ አበባ በእሳት ሲቃጠል አይተዋል። ዲያብሎስ ከተማውን እያመሰው ነበር። ንጉሡ ወደ ጅቡቲ ሸሽተዋል። ጣልያኖችም እየተቃረቡ ነበር። መላው አገሩ ቅጥ ያጣ ለመሆኑ በመልክተኞቹ ይታወቃል። ከለበሱት ሱሪ በስተቀር ሁሉም ነገር ተወስዶባቸዋል። ሕይወታቸውም የተረፈው ጠመንጃ ባለመያዛቸውና የነበራቸውን በፍቃደኝነት በመስጠታቸው ነበር።

*ስለዚህ ሰውየ ወደ ደብረ ታቦር መምጣት ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ በጋሻው በሚባለው መፅሐፋቸው ዘግበዋል። ገሪማ መሐመድ ኢማምን ካባለሬ ኢማም ብለው ነው የሚጠሩት

በዚህ ሁኔታ እያለን ጣልያኖቹ በሚሰጥር ገበሬዎቹን የሚያስፈራራ ቅስቀሳ ያሰደርጉ ነበር፡፡ እያሌው እጁን ካልሠጠ አውሮፕላኖች እሱ ያለበትን ቦታና አካባቢውን በሙሉ እንደሚደበድቡ ነው፡፡ አውሮፕላኖቹ አንድ ቀን ብቅ እሉ ነገር ግን በምብ ሳይሆን ፓምፍሌት ነበር የሚጥሉት፡፡ አዲስ አበባ መያዙን፤ ጠቅላላው አገሩ እጅ መሰጠቱንና፤ የጣልያኑ ንጉሥ የአቢሲኒያ ንጉሥ መሆኑን የሚገልፅ ነበር፡፡

በመጨረሻም ደጃዝማች እያሌው ለጣልያኖች እጃቸውን ለመሰጠት ወሰኑ፡፡ የወሰኑት ውሳኔ ትክክል ወይም ስህተት ይሆን እኔ ፍርድ መሰጠት የምችልበት ሁኔታ እይደለም፡፡ ውሳኔው የራሳቸው ነው፡፡ እኔ የማውቀው ነገር ቢኖር ደጃዝማቹ ያንን ርምጃ ባይወሰዱ ኖሮ እንደኛችንም በሕይወት እንገኝም ነበር፡፡ ሌላ እማራጭ እልነበረም፡፡

በግንቦት ሰባት ደጃዝማች በፍጥነት ወደ ደብረታቦር ተመለሱ ምክንያቱም ጋሰፓሪኒ ለመልሰ ከሁለት ቀን በላይ መጠበቅ እንደማይችል እሰታውቆ ሰለነበር ነው፡፡ እኔ ለጊዜው ከወይዘሮ ማናህሎሽ ጋራ በመሆን ኤፍራታ ቆየሁ፡፡ ከሳምንት በኋላ ወይዘሮዋ ባላቸውን ሊከተሉ ነው፡፡ ከእኔ ምንም ግፊት ሳይኖር ደጃዝማች ጣልያኖቹ እኔን እንዳይነኩኝ ከጣልያኑ አገረ ገዥ ቃል ማግኘት ፈልገዋል፡፡ ደጃዝማች እኔ በጥይት ተረሸኜ የምገደል ወይም ደግሞ እሰር ቤት ውሰጥ የሚወረውሩኝ ወይም ሌላ እይነት ሰቃይ ያደርሱብኛል ብሰው ፈርተዋል፡፡ እኔ ዶክተር ነኝ እና ያደረግሁት ነገር የለም ሰለዚህ መጨነቅ አያሰፈልግም ብዬ ብከራከርም ሊሰሙኝ እልፈለጉም፡፡ ምናልባትም ትክክል ነበሩ፡፡

በግንቦት እሰራ ሰድሰት ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ተሰተካከሏል የሚል መልከት ከደጃዝማች ከሰማን በኋላ ወደ ደብረ ታቦር መመለሰ ጀመርን፡፡ የጣልያኑ እገረ ገዥ ሰአያሌው የከብር ቃሉን ሠጥቷል፡፡ የእያሌው ሀኪም በምንም አይነት ምንም ነገር አይደርሰበትም እንዲያውም ድንበር ተሻግሮ እንዲሄድ እንደሚረዱ ነው የተነገረው፡፡

በግንቦት በደብረ ታቦር ከተማ በየቦታው በብዛት ቆመውና አየተንቀሳቀሱ ከሚታዩ የኢጣልያ ወታደሮች በሰተቀር ከተማው ከዚህ በፊት እንዳየነው ሌላ ሰውጥ እልነበረውም፡፡ እዲሰ ነገር ያየሁት ቢኖር መንገዶችና ገበያዎች በሚሰቁና በሚያውካኩ የተሰያየ ቀለም ያሰው የሀር ቀሚሰ በሰበሱ ደሰተኛ ወጣት ሴቶች ተሞልቷል፡፡ "ሥልጣኔ" የጣልያኖችን እግር ተከትሎ መጥቷል፡፡



በተጨማሪም ሰዎች ከዚህ በፊት ያልታየ እፍረት የለሽና ወራዳ ባህሪ ማሳየት ጀምረዋል፡፡

በሚቀጥሰው ቀን የሁሰቱ ጦር ከፍሎች ሀላፊ ወደ ነበረው ሜጀር ኡጎሲኒ ቢሮ ተጠራሁ፡፡ የመጀመሪያ ግንኙነታችን የተፋጠጠ አይነትና ከሜጀሩም በኩል ወዳጅነት የጎደለው ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ በተለይም በማስተርጎም ከረዳሁት በኋላ በመካከላችን የነበረው ሁኔታ ተሻሻለ፡፡ የሱ አሰተርጓሚ የሚረባ እልነበረም፡፡ ወደ ቤት ደብዳቤ እንድልክ ረዳኝ በተጨማሪም ሰነበሩት ባለሥልጣኖች ወደ አዲስ አበባ እንድጓዋዝ ሰለሚያሰፈልገኝ ፈቃድ ቴሌግራም እንድልክ ረዳኝ፡፡ ሲጋራዎችም ሰጠኝ፡፡ የሲጋራው ነገር የወዳጅነት ይሁን እጠራጠራለሁ፡፡ ሰሰሰት ወራት ማጨሰ አቁሜ ሰለነበር በጣም ጥሩ ሰሜት ነበረኝ፡፡ ለማንኛውም በደብረታቦር የመጀመሪያው ሲጋራ ጥሩ ጣዕም ነበረው፡፡

የጉዞ ፈቃድ አስኪሰጠኝ በደብረታቦር ያሳለፍኩት ሶሰት ሳምንት የሚሆን እሰልቺ ጊዜ የሜጀር ኡጎሲኒ ጥፋት እልነበረም፡፡ ወዳጅና የሚከበር የሰሜናዊ ኢጣልያ ተወላጅ የሆነው ሰውዬ በሚቻለው አቅም እኔን ሰመርዳት ሞክሯል፡፡ በሰሩ ካሉ መኮንኖች ጋራም ወዳጅነት መሰርቼ ነበር ሁልጊዜ ከኔ ከሚርቀው ከወጣቱ ዶከተር በሰተቀር፡፡

ሚሲዮናውያን ጓደኞቼ ከተማው እንደተያዘ በዚያኑ ቀን ለቀው ሄደዋል፡፡ ሁሉንም ነገር ጥለው እንዲሄዱ ተገደው በፍጥነት ወደ ጎንደር ተወሰደዋል፡፡ ለዚህ ፈጣንና አሰገዳጅ ለቆ መሄድ በዚያን ጊዜ የተሠጣቸው ምክንያት እያሌው ከተማውን ሰለሚያጠቁ ለደህንነታቸው ሲባል ጎንደር መሄድ ነበረባቸው ነው፡፡ ነገር ግን እያሌው እጃቸውን ከሰጡ በኋላ ሚሲዮናውያኑ እልተመለሱም የሚሲዮኑ ማእከሉም ለወታደራዊ ሥራ ተወሰዷል፡፡

# ምዕራፍ ሀያ ሶስት

## መበታተን

ደብረ ታቦር እያለሁ በመሃልና በምሥራቁ የሰሜን ግንባር ከፍል የነበሩ አስተማማኝ ሰዎች አገኘሁ ያም ማለት ራሰ ካሳና ራስ ሙሉጌታ በነበሩባቸው ግንባሮች ነው፡፡ ከሰማሁት ሁሉም ነገር የተረዳሁት የሆነውና የተደረገው ነገር በሙሉ እኛ ላይም እንደሆነው ነበር ለውጥ ቢኖር አሰላለፍና ትብብር እንደኔ ሰዎች ደረጃ አልነበረም፡፡

በመጀመሪያ በህዳር ማለት ነው በአቢሲኒያውያን ዘንድ ትኩስ ስሜትና ፍላጎት ስለነበር በመጀመሪያዎቹ ውጊያዎች አስደናቂ ድሎችን ተጎናፅፈው ነበር፡፡ ወደ ሀያ መድፎች ብዛት ያለው የአውቶማቲከ መሳሪያዎች ቁጥር፤ ጠመንጃዎችና ጥይቶች በኢትያጵያውያን እጅ ወድቋል፡፡ በራሰ ካለ በኩል አድዋን መልሶ መውሰድና በራስ ሙሉጌታ በኩል ደግሞ መቀሌን ማስመለስ የጊዜ ጉዳይ ብቻ መስሎ ነበር፡፡ በጦሩም በኩል ጣልያኖች የያዟቸውን ቦታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለቀው እንደሚሄዱ ጥርጣሬ አልነበረም፡፡

ነገር ግን የጦር ሚኒስትሩ ራሰ ሙሉጌታ ለሥራው ብቁ አልነበሩም ታማሚና ሽማግሌም ነበሩ፡፡ የመምራት ችሎታም አልነበራቸውም ስለ ዘመናዊ ጦርነትና ውጊያ አውቀቱም አልነበራቸውም፡፡ እንደላቸው ከሆን ሥራውን ለሌላ ሰው ሠጥተው ወደ ገዳም ቢሄዱ ይቀላቸው ነበር፡፡ ግን ሥራው በግድ ነው የተሠጣቸው፡፡ ለምን የሀገሩ ሰዎች ይህን አንዴት ሲረዱ አልቻሉም በተለይም ለሥራው ብቁ የሆኑ ሌሎቸ አዛዦች እያሉ?

ከአዲስ አበባ የሚመጣው ጥቃት እንዳትፈፅሙ ዝምብላችሁ ጠብቁ የሚለው ትዛዝ ተሰማምቷቸዋል፡፡ ለሽማግሌው የሚመች አልጋ ላይ ተኝቶ ማደሩ ጥሩ ነገር ነበር፡፡ የነበሩት ደህንነቱ የተጠበቀ በአምባ አራዶም በሚገኝ ዋሻ ነበር፡፡ ዋሻው እንደ መኖሪያ ቤት ተደራጅቶ ስለነበር የጎደላቸውም ነገር አልነበረም፡፡ ይህ አይነቱ ሰላም ለረዥም ጊዜ በቆየ ቁጥር ለራስ ሙሉጌታ ጥሩ ነበር ያ ግን ከብዙ ወራቶች በኋላ ጣልያኖቹ አረፍትና ምቾቱ በቃ እስኪሉ ድረስ ነበር፡፡



ከዚያ ግን ተረሰቶና ተንቆ የነበረ አንድ ነገር መታወቅ ጀመረ፡፡ የወታደሮቹን ስሜት ለመጠበቅ የተደረገ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ የጠላትን ፕሮፖጋንዳ በተጋነነ ሁኔታ መቀበል ጀምረዋል፡፡ ለጦሩ የሚበቃ ቀለብም አልተዘጋጀም፡፡ የጦሩ የጤንነት ሁኔታ ጦርነት ለመዋጋትና ለማሸነፍ ወሳኝ ነገር መሆኑም ተረስቷል፡፡

በተጨማሪ ደግሞ ውነተኛ ባልሆነ ተስፋና መረጋጋት ስሜት ራሳቸውን ሞልተዋል፡፡ “ጣልያኖች እንደዚህ ያለ ጠንካራ የአቢሲኒያ ጦር ማጥቃት አይችሉም፡፡ ጀኔቫ የሚካሄደው ውይይት ደግሞ ውጤታማ የሆነ ኢጣልያን የማግለል ውሳኔ ይሰጣል ስለዚህ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ አውሮፕላኖቹ ጭጭ ይላሉ ጠላትም ለሰላም ይደራደራል” የሚሉ ተስፋዎች ነበሩ፡፡

የዚህ ሁሉ ምከንያት ውጤት የማይቀር መከራና ውድቀት አስከተለ

እንግዲህ አንድ ለው ሽማግሌው ሙሉጌታ ላይ ፍርድ ከሚሰጥ ዝም ብሉ ቢያማርር ይሻለዋል፡፡ በርግጥም በራሳቸው ሰዎች በችኩሎቹ አሮሞዎች እጅ ወድቀው ሰቃይ ከሚደርስባቸው የደረሳቸው ዕጣ የተሻለ ነበር፡፡

የራስ ካሳ ጉዳይ እንደ አቢሲኒያውያን ፍርድ አሰጣጥ በጦር አዛዥነት ከመጣ ዜሮ ነበሩ፡፡ ወታደር ከመሆን ይልቅ ቄስ ሆነው ቢያገለግሉ ይሻላቸዋል ይሉ ነበር፡፡ በአጠገባቸው ግንባር እንደነበሩት እንደ ራስ ሙሉጌታ የራስ እነሳሽነት የላቸውም ነበር፡፡ በጠቅላላው ጦርነት ጊዜ ምንም አይነት ውሳኔ በግላቸው ወሰነው አያውቁም ይባላል፡፡ በሳቸው ፋንታ ወይም ንጉሡ አለዚያም ራሰ ሰዩም ነበር ውሳኔ የሚሰጡት፡፡ ከንጋቱ ጀምሮ አስከ እኩለ ቀን ድረስ ራስ ካሳ ቁጭ ብለው ዳዊት ነበር የሚደግሙት፡፡ በጣም አሰፈላጊና ወሳኝ ጉዳዮች ቢኖሩ እንኳን ዳዊት በሚደግሙበት ጊዜ መረበሽ የለባቸውም፡፡ በቅዱሳን በአላት ቀኖች ምንም አይነት ጠቃሚ ሥራ አይሰራም ነበር፡፡ በየወሩ ደግሞ እነዚህ በአላት በተከታታይ ነበር የሚመጡት በእምስተኛው ቀን፡ በለባተኛው፤ በአሥራ ሁለተኛው፤ በአሥራ ዘጠኝ፤ በሀያ አንድ፤ በሀያ አራት፤ በሀያ ሰባት እና በሀያ ዘጠኝ ይውላሉ፡፡

ለባ ሺ የሚሞላው የራስ ካሳ ሠራዊት ስነ ስርአት አልነበረውም፡፡ የአካባቢው ገበሬዎች ይዘረፉሉ ቤታቸው ፈርሶ ለማገዶም ይሆን ነበር፡፡ የማጥቃት ርምጃ አንዳይወሰዱ ቢታዘዙም ብዛት ያለው የጦር ከፍል መሪዎች በራሳቸው እነሳሽነት እጠገብ ወዳሉ ሰፈሮች ይሄዱ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜም ከጠላት ጋራ ይጋጩ ነበር፡፡

ሌላው የሚባለው ደግሞ ራስ ካሳ አንድ ወይም ሁለት ብር ከሚያወጡ ወታደር በረሃብ ቢሞት ማየት ይቀላቸው ነበር፡፡ የጦርነቱ ካዝና በመቶ ሺ የሚቆጠር ብር የያዘ ነው፡፡ ካዝናው በሰምንት ፀሀፊዎች ነበር የሚጠበቀው፡፡ ፀሀፊዎቹ ለየግላቸው ሆነው ነው የሚሠሩት ያ ማለት ቀላል ወይም ትልቅ ግምት የማይሠጠው ወጭ አንኳን በሰምንት የተለያዩ መዝገቦች ላይ መሰፈር ነበረበት፡፡ አንድ ፀሀፊ ከጎደለ ደግሞ ምንም አይነት ክፍያ አይደረግም ነበር፡፡

ረሃብ በሽታ በተለይም ፈንጣጣና ተቅማጥ የራስ ካሳን ሠራዊት ከማንም ሠራዊት በላይ ከራስ ደስታ ሠራዊት በስተቀር በጣም ነበር የወረረው፡፡ አንደዚህ ሆኖ በሺ የሚቆጠር ብር በራስ ወዳዱ ሰውዬ አልጋ ስር ተቀምጦ ነበር፡፡ ብሩ ብዙ የተራቡ ሰዎችን በመመገብ ለታመሙ ሰዎችም አርዳታ መስጠት በቻለ ነበር፡፡ ውድም ቢሆን የሚሸጥ ምግብ ነበረ፡፡

በርግጥ የራስ ካሳ ሠራዊት ውደቀት እንደ ራስ ስዮም ያስ ብልህ አማካሪ ባይኖር ኖሮ ቀደም ብሎ ነበር የሚመጣው፡፡ ራስ ሰዩም ራሳቸው ዋና አዛዥ እለመሆናቸው የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ ስዮም ልምድ ያላቸው ፈጣን ከማሰብ ችሎታ ጋራ ቆራጥ የሚከበሩና ተወዳጅ የጦር መሪ ነበሩ፡፡ ስዩም መሪ ቢሆኑ ኖሮ ከግድ የለሹ ቄሰ ቢጤ ራስ ካሳ የተሻለ ውጤት ያመጡ እንደነበር ግልፅ ነበር፡፡ ራስ ካሳ በነበራቸው የመንገብገብ ባህሪ ወላዋይ የሚርበተበቱና አና ግድየለሽ በመሆናቸው ይጠሉ ነበር፡፡

ያልተጠበቀ የጠላት ማጥቃት በህይለኛ ግፊትና በተቀናጀ ከበባ በምሥራቅ በኩል ሲመጣ የራስ ካሳ ሠራዊት በጀግንነት ነበር የተዋጋው ግን ሙሉ ሰሜት አልነበረውም፡፡ መከበባቸው መቃረቡን ሲያውቁ ደግሞ የማይቀረው መበታተን ተጀመረ፡፡ ከዚያም አንደ ራስ አምሩና አንደ ደጃች እያሌው ሠራዊት በተከዜ በኩል ሽሽት ተጀመረ መጠኑ ግን ተሰምቶ የማይታወቅ አይነት ነበር፡፡ ረሀብ በሽታና ድካም ከውሰጥ በኩል፤ የሠለጠነው ሠቆቃ ከአየር ላይ፤ የተናደዱ ገበሬዎች በጎን በጎን፤ አሰቸጋሪው ምድር ከእግር ስር እንዲህ አይነቱ የመከራ ብዛት በአንድ ቦታ በአንድ ላይ ሲከሰት የሚያስከትለውን ውጤት ማን ነው መገመት የሚችለው?

ጥቂት ወታደሮች አስከትለው ራስ ካሳ በሌሊት ጋልበው ማምለጥ ችለዋል፡፡ ነገር ግን ሲንገበገቡለት የነበረው ሰንት የተራቡና የተቸገሩ ወታደሮች መርዳት የሚቸለው ያ ሁሉ ገንዘብ በየመንገዱ ተበትኖ የገበሬዎች ሲሳይ ሆኗል፡፡



በንጉሡ የመጨረሻው ውጊያ ጊዜ በሚታየው ድራማ ተሰፋ የቆረጡት ሁኔታውን በትከከል ይሁን በስህተት አሳዛኝ ነው ያሉት ራስ ስዩም በጦርነቱ ከመሳተፍ እምቢ ብለው አንደነበር ይነገራል፡፡ ውጊያውን ከፍታ ያለው ቦታ ላይ ሆነው መመልከት ብቻ በቅቷቸዋል፡፡

ጦሩ ወደኋላ አንዲመለስ ሲደረግ የገበሬዎች ማጥቃትና ሽብር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ ፊታውራሪ አዮ የተባሉ ሰው ንጉሡ በነበሩበት ውጊያ ከተካፈሉ በኋላ ከደብረ ታቦር የሁለት ቀን መንገድ ወደሚሆነው ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ሰማዳ ሽሽት ጀመሩ፡፡ ሰውዬውና ሶስት መቶ የሚሆኑት ወታደሮቻቸው እየተዋጉ ነበር ማለፍ የቻሉት ግን የሰማዳ ደንበር ላይ ሲደርሱ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ ገበሬዎች ፊታውራሪውንና ወታደሮቹን ለመዝረፍ ይጠብቁ ነበር፡፡ ከቤተከርሰቲያን ጀርባ መሽገው ከተቀመጡ በኋላ ፊታውራሪ ለገበሬዎቹ መልከት ላኩ፤ ማንነታቸውን ገልፀው ወደ ትውልድ ቦታቸው ያለምንም ችግር አንዲያልፉ ጠየቁ፡፡ የተሠጠው መልሰ ግን ፊታውራሪውና ወታደሮቹ ከለበሱት ሱሪና ሸማ በሰተቀር ጠመንጃና ጥይት ሆነ ሁሉንም ነገር እንዲያሰረከቡ ነበር፡፡ አዮ ለማሰረከብ ሳይሰማሙ ሲቀሩ ገበሬዎቹ ማጥቃት ጀመሩ፡፡ ፊታውራሪው በያዟቸው ጠመንጃዎችና ከውጊያው በማረኩት ሁለት አውቶማቲክ መሳሪያዎች መልሰ መስጠት ጀመሩ፡፡ ከቤተ ከርሰቲያኑ ፊት ለፊት በሜዳው ላይ ሀይለኛ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ ገበሬዎቹ መንገድ መልቀቅ ጀመሩ፡፡ ሰድሰት መቶ የሚሆኑ ሰዎቻቸው ከሞቱ በኋላ የህገራቸውን ሰዎች ለመርዳት ፍቃደኛ ሆኑ፡፡

ጦሩ ከተበተነ በኋላ እንደዚህ አይነቱ አጋጣሚ እንግዳም አልነበረም፡፡ ስለ አቢሲኒያውያን የሰማሁትን የጀግንነት፤ የድፍረትና ሞት አይፈሬነት ብፅፍ በብዙ አሰገራሚ ይዘቶች ብዙ መፅሀፍቶች ይሞላሉ፡፡ በጣም አሰተማማኝ የሆኑ ጥቂት ምሳሌዎችን መጥቀስ አፈልጋለሁ፡፡

በራሰ ሙሉጌታ ሠራዊት ሥር የነበሩ የከምባታ ተወላጅ ወታደሮች ቡድን በመቀሌ ባለው የጣልያኖች ካምፕ ጎን በሚገኝ ዋሻ ብዙ ቀለብና ሌላም ንብረት ጨምሮ እንደሚገኝ ይሰማሉ፡፡ ከአዛዦቻቸው ፈቃድ ሳይጠይቁ በሌሊት ሾልከው በመውጣት የማይል ርቀት ያለውን ሜዳ ያቋርጣሉ፡፡ ሜዳው በጣልያኖች ባውዛ መብራት በየጊዜው ይፈተሻል፡፡ ሆኖም መብራቱ ሲመጣ ወደ መሬት ተወርውረው ልጥፍ በማለት ሳይንቀሳቀሱ መብራቱን ማሳለፍ ለነዚህ ሰውነታቸው ቀላል ለሆኑ ሰዎች እንደጨዋታ ነበር፡፡

መጥፎው ነገር ሌሊቱ ባለበት አልቆየም፡፡ የከምባታ ወታደሮች ከጦር ካምፑ ስር ሲደርሱ የንጋት ኮከብ መውጣት ጀመረች፡፡ ሲያዳምጡ ምንም ድምፅ የለም፡፡ ከፊት ለፊታቸው ግን ባለ ሾህ የሽቦ አጥር ነበር፡፡ ምንም የያዙት መቁረጫ መሳሪያ ስላልነበራቸው አጥሩ ለነሱ የሚጣስ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ለትንሽ ሰከንዶች ግራ መጋባት ተፈጠረ ከዛም በሹክሹክታ ለአጭር ጊዜ ውይይት ከተደረገ በኋላ ድምፅ የሌለው በመቶዎች የሚቆጠሩ እጆች መሬቱን መጫር ጀመሩ በአጋጣሚ መሬቱም ቀለል ያለ ነበር፡፡

ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ሁሉም ከሽቦው አጥር ስር በቆፈሩት መሬት በኩል እየተሳቡ አለፉ፡፡ ጠመንጃቸውን ትከሻቸው ላይ አድርገው ጩቤዎቻቸውን በጥርሶቻቸው ነክሰው ይዘው እየተሳቡ ጋራውን መውጣት ቀጠሉ፡፡ ጋራው ላይ ዋሻዎች በረድፍ ሜትሮች ከፍታ ባለው ጉብታ ላይ ይታያሉ፡፡ አንዱ በአንዱ ላይ እየተረማመዱ የሰው መሰላል ላይ በመውጣት በያዟቸው ጩቤዎች ጠባቂዎችን ጭጭ አደረጉ፡፡

ዋሻዎች ውስጥ ያለውን ለማየትና የሚመረጠውን ለመምረጥ አሳት አበሩ፡፡ በመጨረሻም ከባድ ከረጢቶችን ይዘው ወጡ፡፡ ዱቄት፣ ስኳር፣ ዘይት በጠርሙስ፣ ጥይቶች ካኪ ዩኒፎርም ሌሎችም ብዙ ነገሮች ይዘዋል፡፡ በትከሻቸው ደግሞ ሶስት ወይ አራት ጠመንጃዎችን ተሸክመዋል፡፡ ነገር ግን የቀን ብርሃን ወጥቷል የተዘረፈው ንብረት ቀርቶ ራስን ማዳን ከተፈለገ ወጥቶ በሜዳው በኩል መሄድ የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ ያሰው አማራጭ ሌሊቱ እስኪመጣ መጠበቅ ነው፡፡ ከዋሻዎቹ ወደ ጦር ካምፑ የሚወስደውን ትንሽ መንገድ ለአንድ ቀን ዘግተው መያዝ ይችላሉ፡፡ ውሀ ለማግኘት ግን ምንም እድል የለም ነገር ግን ስለዛ ምን አሰጨነቃቸው?

ውሎውን ብዙ የጠላት ጥቃቶችን መቋቋም ነበረባቸው ከአውሮፕላኖቹ የሚተኮሰው አውቶማቲክ መሳሪያ ጥይቶችን አረበረበባቸው እነሱ ግን በከረጢት ከተሞሉት ዱቄት ጀርባ ስለመሸጉ ግድም አልሠጣቸውም፡፡

መምሸት ሲጀመር ጋራው በነጭ ዱቄት ተሞልቷል፡፡

ከሰአት በኋላ ሲሆን አጥቂዎቹ አቆሙ፡፡ የታሰበው ሰዎቹን በረሃብና በውሃ ጥም የግድ እንዲወጡ ማድረግ ነው፡፡ በመጨረሻም የከምባታ ተወላጆቹ የናፈቁት ሌሊት ሲመጣ የጣሊያኖች ባውዛ መብራት ሰዎቹ በመጡበት መንገድ በኩል ያለማቋረጥ ይበራ ጀመር፡፡ እንደዛም ሆኖ እጃቸውን አልሰጡም፡፡



በፀጥታ መሬት ለመሬት እየተሳቡ በመጡበት ሳይሆን በጋራው በሌላ በኩል መብራት እልፎ እልፎ በሚበራበት ቦታ መሄድ ጀመሩ፡፡ ትላንትና ማታ እንዳደረጉት ሁሉ በአጥሩ ስር ቆፍረው መሹለክ ጀመሩ፡፡ የመጨረሻው ሰው በአጥሩ ስር ሾልኮ እንደጨረሰ ተነቃባቸው፡፡ ወዲያውኑ ጫካው በእንቅስቃሴዎቸ ተሞላ፡፡ ጠመንጃዎች አውቶማቲክ መሳሪያዎች ይተኩሱባቸው ጀመር መድፉም አልቀረም፡፡ ነገር ግን ድምፅ እንጂ ትንሽ ጉዳት ነው የሚያደርሰው፡፡ ሰዎችም ነብሴን አውጭኝ ብለው በሜዳው ተበታትነው መሮጥ ቀጠሉ፡፡

ወዲያውኑ ከጠምንጃ ተኩስ ርቀት ውጭ ሆኑ እራሳቸውንና የዘረፉትን ማዳን ቻሉ፡፡ ለነሱ የተዘረፈው ነገር የህይወት ያህል ጠቃሚ ነበር፡፡ አስር ሰዎች ወደኋላ ቀርተዋል፡፡ ስንት ሰው ይቁሰል ስንት ሰው ይሙት ማንም የሚያውቅ ሰው የለም፡፡

ጦርነቱ እንደተጀመረ የደጃዝማቸ አያሌው ወንድም ደጃዝማች እድማሱ የጣልያኖች ጓደኛ ናቸው አገራቸውንም ለመክዳት ከጣልያኖች ጋራ እቅድ አላቸው ተብለው ተከሰው በንጉሡ ትዕዛዝ ለብዙ ሳምንታት እንዲታሰሩ ተደርገው ነበር ሆኖም ምንም ማስረጃ ስላልተገኘ በነፃ ተለቀቁ፡፡ ይህንን የሐሰት ክስ መሆኑን ለማስመስከር እድማሱ ለአባት አገራቸውና ለንጉሡ ታማኝነታቸውን የሚያሳዩበት አጋጣሚ እየጠበቁ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመጀመሪያውም ለከሱ ምክንያት የሆኑት ራስ ካሳ የእድማሱን የየጁ ግዛት ይመኙ ስለነበር እድማሱ ስማቸውን ለማደስ የሚፈልጉበትን አጋጣሚ ሁሉ ይከለክሏቸው ነበር፡፡

እንዲህም ሆነ፡፡ አንድ ትንሽ የሆነ የጣልያኖች ካምፕ ሁልጊዜ አቢሲኒያዊያን ላይ በርቀት እየተኮሰ ያስቸግር ነበር፡፡ ይህን የመድፍ ተኩስ በብዛት የሚቀበለውም የእድማሱ ሠራዊት ነበር ለሰዚህ እድማሱ የጣልያኑን ምሽግ ጥሰው ለመግባት ራስ ካሳን ደጋግመው ፈቃድ ጠይቀው ነበር፡፡ ራሰ ካሳ ግን የሰው ሕይወት ቢጠፋ የሚሰጠው ጥቅም የለም በማለት ከለከሏቸው፡፡

ደጃዝማች እድማሱ ራሳቸው ወሰኑና አንደ ቀን በንጋቱ ላይ አንድ ሺ የሚሆነውን ሠራዊታቸውን እንዲያጠቃ ትዛዝ ሠጡ፡፡ እራሳቸውም ቢሆን በጣልያን የተሰራ አውቶማቲክ መሳሪያ ሲተኩሱ ዋሉ፡፡ እኩለ ቀን ሲሆን ተራ በተራ ያደረጉት የማጥቃት ሙከራ አልሰራም ራሳቸው እድማሱ በመሳሪያው ግለት ምክንያት እጃቸው ውሃ መቋጠር ሲጀምር አጥቂዎቹ ጥቃቱን የማቆም አዝማሚያ ላይ ነበሩ፡፡

ራስ ካሳ ውጊያው ትርፍ የሰውም ብሰው ነው ያሰቡት ያውም አጠገባቸው ያሉ ሰዎቻቸው ተጨማሪ ሀይል ሰርዳታ እንዲላክ ቢወተውቷቸውም:: ሰዎቹ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻቸውን ለመርዳት ዝግጁ ነበሩ:: "አይሆንም!" ራስ የፈለጉት ጠቅላላው አጥቂ ጦር ከአዛዡ ጋር እንዲደመሰሱ ነው:: አድማሱ የራስ ካሳን ትዛዝ መጣስ ማሰት ምን ማሰት እንደሆነ ማወቅ አለበት::

ያም ሆኖ ደጃዝማች አድማሱ ማቆም አልፈለጉም:: ተስፋ በሌሰው ሁኔታ ይመጣል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው ተጨማሪ ሀይል አሰመምጣቱን ሲያዩ የየጁ ጎበዞች ሰዎቻቸውን ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥቃት እንዲሞክሩ ያበረታቱ ጀመር::

ተሳካላቸው:: ልክ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ከመሆኑ በፊት የመጀመሪያው የአቢሲኒያ ሠራዊት የካምፑን አጥር ጥሶ ገባ:: የጨበጣ ውጊያ ነበር:: አንድ የበታች መኮንን ሀያ የሚሆኑ ወታደሮችን ይዞ እየተኮሰ ያስቸገረውን አንድ መድፍ ለመውሰድ ወስኗል:: መድፉ በጥሩ የተጠበቀ ቦታ ነበር:: መኮንኑ ሰዎችን ሰበሰበና ከሁለት ቦታ ከፍሎ በጎን በጎን ካሰሰፈ በኋላ ራሱን በመሀከል አደረገ::

"አሁን እኔ ፊት ለፊት ወደ መድፉ አፈሙዝ ስሮጥ እናንተ በጎን እንድታጠቁ:: አትፍሩ! የሚተኮሰውን እርሳስ(ጥይት) እኔ አቀበሰዋለሁ!!"

ያን ትዛዝ ከሰጠ በኋላ ቀጥታ ወደ መድፉ አፈሙዝ ፊት ሰፊት ሮጠ መድፉም ሰተኩስ ተዘጋጅቶ ስለነበር ተተኮሰ ሌሎቹ ወታደሮች እየጮሁ ወደፊት በመሮጥ መድፉን ሲተኩሱ የነበሩትን ስድስት የጣልያን ወታደሮች ጭጭ አደረጓቸው ነገር ግን አቢሲኒያዊው መኮንን አዛዣቸው ሳይመሰስ ሰዘላለም ሄደ::



# ምዕራፍ ሀያ አራት

## በመጨረሻም ሥልጣኔ
## ድንገተኛ አውሮፕላን ማረፊያ ያለመኖር

ግንቦት አሥራ ሁሰት የተከበሩ ፒሪዞ ቢሮሊን ተቀበልን:: ቢሮሊ የምድር ጦር ጀኔራል ነው የባዶሊዮ ቀኝ እጅ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ የአማራ ገዢ ተብሎ ተሰይሞ መኖሪያውን በጎንደር አድርጓል:: የደብረ ታቦሩ ጉዞው ጦሩን ሰመጎብኘት ነው::




ጀኔራል ፒሪዞ ቢሮሊ
የኤሪትራ ጦር አዛዥ

በጀኔራሉ አዝ ስር ከነበሩት
የኤሪትራ ተወላጆች ጦር
ግማሹ ጦር በመጀመሪያዎቹ
ቀናት በመከዳት ወደ
ኢትጵያውያን ወገኖቻቸው
ተደባልቀዋል ተብሎ ተዘግቧል

በሚቀጥሰው ቀን ሰውየው ተቀብሎኝ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች መናገር እንድችል ተፈቀደልኝ:: ጀኔራሉ ያለሁበትን ሁኔታ በመገንዘብ ዕርዳታ እንደሚያደርግልኝ ቃል ገባልኝ:: በሚቀጥሰው ቀን ወደ ጎንደር አብሬው በመሄድ ከዚያ በኋላ በወታደራዊ አውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ እንደምሄድ ነው የታሰበው::

ለአንድ ሰአት የሚሆንም ስለ ጦርነቱ ቁጭ ብሰን ተወያየን:: ጀኔራሉ ማወቅ የፈሰገው በአቢሲኒያውያ በኩል ሁኔታው ምን እንደነበር ነው:: በተጨማሪም አዲስ አበባ ከተማ የደረሰውን ውድመት ነገረኝ:: ፒሪዞ ቢሮሊ አዲስ አበባ ከገቡት የመጀመሪያው ነው በተሠረቀ በንጉሡ መኪና ሆኖ ነው

የገባው፡፡ ከአየር ላይ የተነሳ ፎቶግራፍም አሳየኝና ስመለከት ቤቴ አንዳልፈረሰ ማየት ቻልኩኝ፡፡

አንግዲህ ነፃ የምሆንበት ሰአት አየመጣ ነው፡፡ አጭር ቀን ብቻ፡፡ ከተኩስ ልውውጥ ከልል ውጭ አሆናለሁ አና ህይወቴን መጠበቅ አችላለሁ፡፡ ጀኔራሉን ትቼ ስወጣ በጣም ደሰተኛ ነበርኩ፡፡ ሁሉም ነገር በትክከል ከሄደ በአሥራ ስድስት በሰቅቅኩ ከሰባት ወራት በኋላ ተመልሼ አዲስ አበባ አንደምገባ ተስፋ አድርጌያለሁ፡፡

በሰኔ አሥራ አምስት ገና ፀሐይ ሳትወጣ ተዘጋጅቼአለሁ፡፡ ሻንጣዬ የያዘው ነገር ቢኖር ሶስት የፂም መላጫ ከሶስት ምላጮች ጋራ፣ ሳሙና፣ የአጅ ፎጣና የተጠቀሰለ ብርድ ልብስ ነበር፡፡

ስንብቴ ከደጃዝማች አያሌውና ከሁሉም ወዳጆቼና የጦርነት ጓደኞቼ ጋራ ከጠበቅሁት በላይ ከባድ ነበር፡፡ እይናቼ እያነቡ ቃላቶቼም ጉሮሮዬ ውስጥ አየተሰነቀሩ ነበር፡፡ አብረን ደስታውን ቁጥር ስፍር የሌለውን መከራና ችግር ያሳለፍን ሰዎች አንደገና እንገናኝ ይሆን? በዚህ በከፉ ቀን መልሶ መገናኘቱ የማይታመን ነገር ነው፡፡

ደጃች አያሌው መሄዴን ሲገነዘቡ ተመልሼ መጥቼ የሳቸው ሀኪም እንደሆን ቃል አስገቡኝ፡፡ እሱም እኔ የምመለስበትን ሁኔታ ደጃዝማቸ ካዘጋጁ ነው፡፡ ልክ ስንለያይ ብዙ መቶ የማር ተሪዛዎች ለመንገድ እንዲሆን ብለው ሰጡኝ፡፡ አንደማፈር ብለው ገንዘቡን ሲሰጡኝ ሀዘኔታ ተሰማኝ፡፡ ቢችሉ ከዚህ እጥፍ ሊሰጡኝ አንደሚችሉ አውቃለሁ፡፡

የደጃዝማች ሚስት ወይዘሮ ማናህሎሽ የጣታቸውን የወርቅ ቀለበት አውልቀው ለማስታወሻ አንዲሆን ብለው ሠጡኝ፡፡

አቶ ማሞና ባለቤቱ እንደ ሕፃን ልጅ ያነቡ ነበር፡፡ ትንሿ አፀደ ከእግሬ ላይ ተጠምጥማ

"አባባ ጥሎን አይሄድም!!" እያለጭ ትጮህለች፡፡

ከዚያ ቀጥሎ ሃምሳ የሚሆኑት የደጃዝማች የቀሩት የግል ዘቦች በአከብሮትና በፀጥታ እየመጡ ጉልበቴን ወይ እግሬን ይስማሉ፡፡ በዚህ ሁሉ መሀል የከዳኋቸው መስሎ ተሰማኝ ነገር ግን መሄድ ነበረብኝ ግዴታዬ ነበር፡፡

ጀኔራሉና ተከታዮቹ ስንብቱን ትቼ ከመልቀቄ በፊት ተነስተው ሄደዋል፡፡ የጭነት መኪና ከአስር ወታደሮች ጋራ ሆኖ ይጠብቀኝ ነበር፡፡ ሾፌሩ ባሰበት ጋቢና በኩል ዘልዬ ገባሁ ማርሽ ተቀየረ መኪናው ማጓራት ጀመረ ከዚያም ጓደኞቼና ከተማው ከጋራው ጀርባ ተሰወሩ፡፡




ጉዞው ከመጀመሪያው አስቸጋሪ ነበር፡፡ ለብዙ ቀን ሲዘንብ ሰንብቷል፡፡ እየደጋገምን በጭቃ እየተያዝን ሁላችንም አየወረደን አንረዳ ነበር፡፡ ትልቁን የርብ ወንዝ በአፄ ፋሲል ድልድያ ላይ ከተሻገርን በኋላ መንገዱ ደረቅና ለስላሳ ሆነ፡፡ ጉዟችንም ይፋግን አልፎ በአሰልቺው የደምቢያ ሜዳ በኩል ቀጠለ፡፡ ለምሳ በጣና ሀይቅ ዳርቻ አጭር አረፍት ካደረግን በኋላ አንደገና ጉዟችን ቀጠልን፡፡

አሁን ደግሞ የመንገዱ ችግር አንደገና መጣ፡፡ ዳገታማ ነው፡፡ ዝናብ መጣል ጀመረ፡፡ መኪናው ይንሸራተታል ወይም ጭቃ ውስጥ ይቀረቀራል፡፡ ጎማ በየተራ አየተነፈሰ ጉዟችን አራዘመው፡፡ ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ሲሆን በጎንደር የወታደር ካምፕ ግቢ ውስጥ ገባን፡፡ እብረውኝ የተጓዙት ሰዎች መኖርያ ቦታቸው ስለሆነ አያንዳንዳቸው ድንኳን አግኝተዋል፡፡ ሌሊት ስለሆነ ሁሉም ሰለተኛ ለኔ ማደሪያ ሆቴል አልተገኘም ሰለዚህ ብቻዬን የቀረውን ሌሊት ከጭነት መኪናው ጀርባ አሳለፍኩ፡፡ ጭቃ በጭቃ ሆኛለሁ በድካም ሙትት ብያለሁ ለማንኛውም ጎንደር ገብቻለሁ፡፡ ቀስ በቀስ ወደ ግቤ እየተጠጋሁ ሰለሆነ ደስተኛም በመሆኔ እንቅልፍ አንዲወስደኝም አደረግሁና እንደወደቀ ግንድ ተኛሁ፡፡

ቀረብ ያለው የአውሮፕላን ማረፊያ ከጣና ሀይቅ አጠገብ የሚገኝ ጎርጎራ የሚባል ቦታ ነው፡፡ በአሥራ ስድሰት ማምሻውን ወደ ጎርጎራ ልንሄድ ነው፡፡ በተመደበልኝ አስጎብኝ እርዳታ ቀኑን የፈረሱትን በመሀከለኛው ከፍለ ዘመን የተሠሩ የጎንደር ቤተመንግስት ግንቦች ስጎበኝ ዋልኩኝ አለዚያ ከተማው አንኳን ምንም የሚታይ ነገር የለውም ነበር፡፡

በጊዜ ብዛት የግንቡ ቅስቶች ጡቦችና ሲሚንቶው ተጎድቷል፡፡ የፈራረሱት ግንቦች ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ አንዳለ እንደሚናዱ ነው፡፡ እንደተረዳሁት ከሆነ ደግሞ ጣልያኖቹ ግንቦቹን ሰማደስ ምንም ፍላጎት የላቸውም፡፡

በመሀከለኛው ከፍለ ዘመን የአቢሲኒያ መናገሻ ከተማ ስለነበረው ጎንደር ያን ሁሉ ከሰማሁ በኋላ ከተማውን ሳየው አንደጠበቅሁት ሰላላገኘሁት በጣም ነው ያዘንኩት፡፡ ጠቅላላው ጎንደር ያልፀዳና ያረጀ ሆኖ ነው የታየኝ፡፡ ጣልያኖቹም ከተማውን ከጎንደር አርባ ኪሎሜትር ርቀት ወደሚገኘው ወደ ጎርጎራ ሰመውሰድ ያቀዱ ይመስላል፡፡



የጎንደር ግንብ ከጦርነቱ ከጥቂት አመታት በፊት የተነሣ ፎቶግራፍ (Agenore Frangipani, l'equivoco Abissino)



ለምሳ የተጋበዝኩበት የጄኔራሉ ፅሕፈት ቤት በሚገርም ማረፊያና መናፈሻ ቦታ አድሜ ባላቸው የወይራና የፅድ ዛፎች ባሉበት ነው ያረፈው:: በመሀሉም የፈራረሰው የመዝናኛው ግንብ አለበት:: ባለሁለት ፎቅ የሆነው የመዝናኛው ግንብ በየወለሉ አዳራሽ ያለው ሲሆን በድሮ ጊዜ ለመዋኛ የሚያገለግል የውሃ ፊሰስ ላይ ነበር የተሰራው:: አሁን ድረስ የሚያገለግል መሻገሪያ ድልድይ ወደ ግንቡ ያስገባል:: በመሀከለኛው የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን በዳግማዊ አፄ አያሱ ዘመነ መንግስት ወግ የሌለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በዚህ ግንብ ውስጥ ይካሄድ ነበር ይባላል::

ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን ዱቄትና ሌላም ቀለብ የተጫኑ ሁለት የጭነት መኪናዎች ይዘን ወደ ጎርጎራ መንገድ ጀመርን:: ከብዙ ድካም በኋላ በዝናብና በሚያንሸራትት መንገድ ጎማዎች እየተነፈሱብን ከጠዋቱ ሶስት ሰአት ጎርጎራ ደረስን:: እዛ እንደደረስኩ በአንድ ሻለቃና አስር ወታደሮቹ ወዳጅነት የሌለበት አቀባበል ነበር የገጠመኝ:: ሆኖም በጦርነቱ ጊዜ አቢሲኒያኖቹ እንዴት እንደተዋጉ ለማወቅ ታላቅ ጉጉት ስለነበራቸው ንግግር ተጀመረና በመሀከላችን የነበረው ቀዝቀዛ ግንኙነት ቆመ::

በየጊዜው ግን እየደጋገሙ ለውዲኖች ጥሩ ሰዎች አይደሉም እያሉ ያስታውሱኝ ነበር:: እንደ ጣልያኖቹ ከሆነ እያንዳንዱን የሚያገኙትን የስዊድን ዜጋ መስቀል ነበረባቸው:: ያም ሆኖ ጥሩ ምግብና ጥሩ መኝታ ከማግኘት አልተከለከልኩም:: በኋላ እንደተረዳሁት ስዊዲኖችን መስቀል በሌላ መንገድም ሊደረግ ይቻላል ልክ እንደ[1] ግሬታ ጋርቦን የመሰለ ሰው ፎቶግራፍ ከምሽግ ግድግዳ ጀርባ እንደመስቀል ማለት ነው::

ጎርጎራ አውሮፕላን እንደሌለ ተነገረኝ:: በዝናቡም ምክንያት ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ አውሮፕላን የለም:: ግን በነጋታው ከጎጃም የሚመጣ ካፕሮኒ የሚባል አውሮፕላን ይጠብቁ ነበር:: አውሮፕላኑ ከጥቂት ቆይታዎች በኋላ ወደ አስመራ ይሄዳል:: ሜጀሩ ወደ አስመራ እንዲሄድ ለለተፈቀደለት አውሮፕላኑ ለሱ ሲባል ነው ጎርጎራ የሚያርፈው ለኔም እንግዲህ ቦታ አይጠፋም:: አጋጣሚ ሆኖ እኔም የጉዞ ፈቃድ አለኝ:: ሆኖም ማለፊያ ወረቀት አልነበረኝም:: ጀኔራል ቢሮሊ ለኔ ወደ አስመራ ለመሄድ ከፍት ነው ከዛ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንደምችልም ነግሮኝ ነበር::

---

*1.ግሬታ ጋርቦ በስዊድን ሀገር የተወለደች በዘመኑ ታዋቂ የሲኒማ ተዋናይ ነበረች*

ሌሊቱን በሙሉ ሲዘንብ አደረ ጠዋት አስቀያሚና ቀዝቃዛ ነበር:: ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ባለአንድ ሞተር በምብ ጣይ አውሮፕላኑ ሲመጣ እኛ በዝናብ የራሰው ማረፊያ ላይ ወጥተን እየጠበቅን ነበረ::

መንገደኞቹ የአየር ሀይል ጄኔራልና ሁለቱ ረዳቶቹ ፓይለቱና መካኒኩ ከአውሮፕላኑ ወረዱ:: የነበረንን ሃሳብ ነገርናቸው:: ጄኔራሉም ሁለት ሰዎች መውሰድ የሚችልበት ሁኔታ የለም ብሎ መለሰልን:: አንድ ሰው እንኳን ተጨምሮ ተንደርድሮ ለመነሳት አስቸጋሪ ነው አለ:: ሜጀሩ በደግነት ቦታውን ለቀቀለኝ:: ምድሩ በጣም ረጥቦ ስለነበር አውሮፕላኑ የተነሳው በሁለተኛው ሙከራ ነበር::

የጣና ሐይቅ እንደመሰታውት ተዘርግቶ ይታያል ከዚያ ውጭ ግን የቀረውን መሬት ከባድ ደመና ሸፍኖታል:: ምንም ማየትም አንችልም ነበር ነፋሱ ደግሞ አንደማዕበል ነው:: አሰቀያሚ የአየር ጉዞ ነበር:: ቀዘቃዛው አየር በቦምብ መጣያ ስድስት ከፍተቶች በኩል ሰለሚገባ በብርድ ተንሰፈሰፍን:: ወደ ሰሜን ተራሮች አካባቢ ስንደርስ ከደመናው በላይ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ከፍታ መውጣት ነበረብን:: አሰቃቂ ነበር::

ወደ ተከዜ ረባዳ መሬቶች ስንደርስ ደመናው ቀለል ማለት ስለጀመረ ወንዞችንና በጦርነቱ ጊዜ በደንብ የማውቃቸውን የትግራይ መሬቶች ማየት ቻልን:: ነገር ግን እንደገና የኤርትራ ከፍታማ ቦታዎች አስከንደርስ ድረስ ደመና መልሶ ሸፈነ::

በዚህ ጊዜ የአውሮፕላኑ ነዳጅ መጠን በፍጥነት እየቀነሰ እንደሆነ መጠቆሚያው ያሳያል:: በደመናዎቹ አልፈን ከአስመራ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘው አዲ ቋላ ከተማ ስንደርስ ሁለት መቶ ሊትር ብቻ ነው የቀረን:: አውሮፕላኑን እያበረረ የነበረው ጄኔራሉ ያሰው ነዳጅ ያሰብንበት ቦታ ያደርሰናል ብሎ ነው ያሰበው::

እንዴት እና ለምን አቅጣጫው እንደጠፋብን አልገባኝም:: ያውቅሁት ተመልሰን አድዋን እንደገና በሩቁ ስናይ ነው:: የሚታመን ነገር አልነበረም:: በቀጥታ ወደ መጣንበት እዙረን ተመልሰናል:: ካፒቴን ፓይለቱ ደጋግሞ ስለ አቅጣጫው ተናግሮ ነበር ነገር ጄኔራሉ ሊሰማው አልፈለገም::

አድዋ መታየት ሲጀምር በመቶ ሰማንያ ዲግሪ ተመልሰን ዞርን:: መጠቆሚያው በዚህ ጊዜ አንድ መቶ ሊትር ነዳጅ ብቻ መቅረቱን ነው የሚያሳየው:: ያ እንግዲህ አዲ ቋላ የሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ ሊያደርስን ይችላል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የሆነ ነገር ተበላሸ::

*ፑፍ! ፑፍ! ፑፍ!* ከዚያ በኋላ ፍፁም ፀጥታ::



የምንሰማው ነገር ቢኖር የአውሮፕላኑ ክንፍ አየሩን እየቀዘፈ ሲሄድ የሚሰማው ፉጨት ነው:: ሞተሩ ቆሟል::

ነዳጁ አልቋል:: ሀምሳ ሊትር የሚሆን በነዳጅ መያዣው ውስጥ ቢኖርም፤ እኛም አንድ ሺ ሜትር ከፍታ በአየር ላይ ነበርን::

"በፍጥነት እየዘለላችሁ ውጡ!" አለ ጄኔራሉ በጩኸት መሪውን ለካፒቴኑ እየለቀቀ:: በደንቡ መሠረት ሁላችንም ፓራቹት አስረናል::

ቁልቁል ተመለከትኩ በሕይወቴ ከአየር ላይ ዘልዬ ለመውረድ ደፍሬ አላውቅም:: አስቡት እንግዲህ ፓራቹቱ ባይከፈትስ! በፍጥነት ወደ ምድር ወርጄ ብፈጠፈጥ ምን አይነት ሰውነት ነው የሚቀረኝ? አንድ ሰው መሞት ካለበት ምናልባትም ይህ የተሻለ አሟሟት ይሆናል::

"ባላችሁበት ቆዩ:: ይህን ነገር ልቆጣጠረው እችላለሁ" የሚያረጋጋ የፓይለቱ ድምፅ ነበር::

አውሮፕላኑ እየተሽከረከረ ቁልቁል ወረደ:: መሬቱ እየተቃረበ ይመጣል፤ ተከሎቹና ምድሩም እየተለቁ መታየት ጀመሩ:: እኛ ባለንበት ቆመን መሬቱ በኛ ዙሪያ የሚሽከረከር ነበር የሚመስለው:: ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ ሜዳ መታየት ጀመረ::

"ወለሉ ላይ ተኙና አጥብቃችሁ ያዙ አውሮፕላኑን ላሳርፍ ነው"

ሀይለኛ መንጠርና መርገብገብ ነበረ እኔም የሚሽከረከር አውሎ ነፋስ አዙሪት ውስጥ ያሰሁ መስሎ ነው የተሰማኝ:: እርስ በራሳችን እስከንላጋ ድረስ ደጋግሞ መንጠር ቀጥሎም ድንገተኛ መርገብገብ ካደረግን በኋላ ቆምን::

ፓይለቱ ላማሳረፍ ሲዘጋጅ ፍጥነቱን ለመቀነስ ልጓሙን ተረግጦ ነበር ነገር ግን ከፊት ለፊቱ ትልቅ ዛፍ ሲያይ በድንጋጤ ልጓሙን እንደያዘ መሬቱ ላይ አረፍን:: አውሮፕላኑ በቀኝ በኩል ዛፉን መቶ ሰብሮታል በዚህ ምክንያት በቀኝ በኩል የሚገኘው የማቆሚያ ልጓም ተሰብሮአል:: በግራ በኩል ያለው ብቻ ስለሚሰራ አውሮፕላኑ ተሽከርክሮ ካፒቴኑ ወዳልፈለገበት ወደ መጣበት አቅጣጫ በኩል ዞረል:: ወደፊትም በቁጥቋጦና በትንንሽ ዛፎች ላይ በመሄድ ጉድባ ውስጥ ሲደርስ ብቻ ቆመ::

ነገር ግን መጨረሻው ጥሩ የሆነ ነገር ጥሩ ነው ከመጥፎ አደጋም ተርፈናል:: ከያዝነው ስንቅም ጥሩ ምግብ አዘጋጅን:: በአውሮፕላኑ ጥላ ስር ተጠግተን ምግቡን በላን:: ሁሉም የምመኘው ነገር ነበር ::የጎደለኝም አልነበረም::

ወደ አድዋ ከሚወስደው ዋናው ጎዳና ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት የአውሮፕላን ድንገተኛ ማረፊያ ከመረብ ወንዝ አጠገብ መሠራቱን አወቅን:: አልፎ አልፎም አልፈው ከመሄዱ መኪኖች ድምፅ እንሰማ ነበር:: ያካባቢው ተወላጆች መጡ:: የኢጣልያ የመንገድ ሠራተኞችም መጡ:: ከእውሮፕላኑ ሲዘል የተጎዳውን ካፒቴን ተሸከመው መንገዱን በማሳየት ረዱን::

በተጠራው አምቡላንስም ሆነን መጀመሪያ ወደ አዲ ቋላ ከዚያም ወደ ጎራ ቀጠልን:: ጎራ ትልቁ የጣልያኖች የአየር ጣቢያ ነው ከአስመራ በደቡብ አርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ላይ ነው የሚገኘው:: በዚህ ቦታ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ አውሮፕላን እየጠበቅሁ የአብራሪ መኮንኖች እንግዳ ሆኜ ለሁለት ቀናት ቆየሁ:: የዝናቡ ወራት ስለጀመረ የአውሮፕላን በረራዎች ይሰረዙ ነበር:: መጥፎ አጋጣሚ ነበር:: ለኔ የነበረኝ የቀረኝ አማራጭ በአስመራ በኩል ሄጄ ከምፅዋ ጀልባ ይዤ ወደ ጅቡቲ መሄድ ነው:: ነገር ግን እንዴት ብዬ ነው ለጉዞው ይለፍሰ ሆነ ገንዘብ የማገኘው?

ምንም ቢሆን ለአንድ ነገር መውጫ አሰው:: አስመራ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ፈቃድ እስካገኝ ድረስ ለሶስት ሳምንታት መቆየት ነበረብኝ:: በመጨረሻ ይሰፍ ወረቀት ማግኘቴ ከታላቅ ዕድል ነው የሚቆጠረው:: "Nulla Osta" "ይህን ይሰፍ ሰያዘው ሰው ምንም አከል እንዳያጋጥመው" የሚል ፅሁፍ ያለው ይሰፍ አዲስ አበባ ከተያዘች ወዲህ ለሲቪል ሰው ሲሰጥ አምስተኛው ነው:: ሌላ ከፍ ያለ ችግር ሳይፈጠር የምፅዋን ሞቃታ አየር ከተቀበልኩ በሐምሌ አስራ ሰባት አዲስ አበባ እገባለሁ:: ቀናቱን ሳስብ ዘጠኝ ወራቶች አልፈዋል::

በመጨረሻም አዲስ አበባ:: የደረስኩ እለት እየዞርኩ ያየሁት ውድመት የፈጠረብኝን የሀዘን ስሜት ምንም ጊዜ አልረሳውም:: ስለዚህ ጉዳይ ግን ብዙ ሰዎች ስለፃፉ በዚህ ውስጥ መጥቀስ አያስፈልገኝም:: በየመንገዱና በገበያ ቦታ ይርመሰመስ የነበረው ሰው ፤ ባለባቶች ከአጃቢዎቻቸው ጋራ በፍፁም አይታዩም:: የአውሮፕውያን ሠራተኞች ከሆኑት በስተቀር ሁሉም አቢሲኒያኖች የሸሹ ይመስላል::

ቤቴ ውስጥ የቀረ አንድ ነገር የሰም:: ሁሉም ነገር ተዘርፏል::

በደቡብ በኩል ከአዲስ አበባ መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኘው እርሻ ቦታዬ ጋራ ግንኙነት ማድረግ አልተቻለም:: እስካሁን ራቅ ካለው ከእርሻ ቦታው ነው አለ ከሚባለው ከወንድሜ ከዋልደማር ጋራም መገናኘት አልተቻለም:: ጣልያኖቹ ሰዎች እንዲልኩም ሞከሬ ነበር:: በፈቃዳቸው ከሚጓዙ ጀርመኖች ጋራም አብሬ እንድሄደ ብለምንና ብማፀነም ትከሻቸውን



እየገፉ "አይሆንም" ነው የሚሉት:: ሌላ አይነት ሙከራ አደገኛ ነበር:: ያገሬው ሰዎች አውሮፕውያንን እንዳይነኩ የሚል ፅሁፍ ያለባቸው ሊፍሌቶች በአውሮፕላን ተበትነዋል ብለው ሊያፅናኑኝም ሞከሩ::

አዲስ አበባ በቆየሁበት ጊዜ ሁል ጊዜ ማታ ማለት ይቻላል ጣልያኖቹ በጣም በሚፈሩዋቸው ሽፍቶች ከተማው ጥቃት ይደርስበት ነበር:: በነዚህ የአባት አገር ተዋጊዎች እጅ የወደቁ ጣልያኖች አስከሬን ካየሁ በኋላ የጣልያኖቹ ፍርሀት አላስደነቀኝም::

አዲስ አበባ በመጣሁ ከጥቂት ቀናት በኋላ  የኢጣልያ ሆስፒታል ወደሚባለው ቦታ ሔድኩኝ:: በዚያም ለብዙ አመታት የሆስፒታሉ ሀላፊ የነበረ ጓደኛዬን ለመገናኘት ነበር:: በአምቦ መንገድ ላይ በሚገኘው አሁን በጣልያኖች እጅ በሆነው የስዊድን ሚሲዮን ማእከል አጠገብ ደርሼ ነበር:: ማእከሉ ከሆስፒታሉ ጎን ነው የተሰራው::

በድንገት በግራ በኩል ካለው ጉድጓዳ ሰፍራ ጥይቶች እያፏጩ ይመጡ ጀመር:: በማእከሉ ግንብ ጀርባ የጣልያኖቹ አውቶማቲክ መሳሪያም መልስ ይሰጥ ጀመር:: ለማሰብ እንኳን ጊዜ ሳለገኝ በሁለቱ ተኩስ ልውውጥ መሀል መሆኔን አወቅሁ:: ከአንድ ጦርነት ወደ ሌላ ተሸጋገርኩኝ:: ያ ሁሉ ተብሎና ተደርጎ በመጨረሻው ህይወቴም ሊያልፍ ነው ማለት ነው::

በኋላ  አንድ የኢጣልያ መኮንን እየተሳበ መጥቶ አፌን ከፍቼ አዛው ባልቆም እንደሚሻለኝ ይልቁኑ ተከትየው ከሚሸኑ ግንብ ጀርባ እንድጠለል ጮኸብኝ:: ለሶስት ሰአታት ቁጭ ብዬ የተኩስ ድምፅና የጥይቶችን ፉጨት ሳዳምጥ ቆየሁ:: የጣልያኖቹ ካምፓኒ ወጥቶ ለማጥቃት ዝንባሌም አላሳየም ምክንያቱም ከተኩሱ በመገመት የሽፍቶቹ ቁጥር ከሀምሳ በላይ ይሆን ነበር::

በአዲስ አበባ ውስጥ ምቾት ባይኖረውም ለአምስት ሳምንታት ቆይታ ካደረግሁ በኋላ  ከተማውን እንድለቅ ተገደድኩ:: ጣልያኖቹ በግልፅ ስዊድናዊ የሚባል ሰው ማየት እንደማይፈልጉ ነው የነገሩኝ::

ያለኝን ነገር በሙሉ በሁስት ሻንጣዎች አሽጌ ለዘጠኝ አመት የሰራሁበትን ከተማ ለቀቅኩ:: በዚህ ከተማ የተዳርኩበት ቤት የሠራሁበት እና ሁለት ልጆች ያፈራሁበት ነበር:: ተመልሼ የማላያቸው ብዙ ጓደኞችም ነበሩኝ:: በጣም የለመድኩት ሀገር ቋንቋቸውን እንደራሴ አድርጌ የምናገረውና እየወደድኩዋቸው የመጣሁት ተወላጆቸ ለአድሜ ልክ ላጣቸው ነው:: የነበረኝን ገንዘብ በሙሉ ያፈሰስኩበት የእርሻ ቦታዬም ለነፋስና ለውሀ ሊቀር ነው::

በጣም ያሸበረኝ ነገር ግን የወንድሜ ጉዳይ ነበር ምንም ላደርግለት የምችለው ነገር አልነበረም። በዚያን ጊዜ ያላውቅሁት ነገር ከሁለት ወራት በኋላ በርግጠኛነት እንደተረዳሁት ለዘላለም እንደማላየው ነው። ከወንበዴዎች በተተኮሰ ጥይት ሀይወቱ አልፏል። ምናልባትም በግንቦት ወር መጨረሻ አካባቢ ነበር። ብቻውን ተረስቶ ቀርቶ ቁጭ ባለበት ስርአትና ህግ በሌለበት በአርሲ ያለምንም ማምለጫ እርስ በእርስ በሚዋጉ ጎሳዎችና በጨካኝ ወንበዴዎች ተከቦ ነበር።

እኔ ስንት ጊዜ ነው የሞትን ነጭ አይኑን ያየሁት ግን ሕይወቴን እጅና እግሬን ይዤ ያመለጥኩት? ነገር ግን ዋልደማር መሞት ነበረበት ወይ? አጋጣሚ?

እይሆንም! በፍፁም። በአጋጣሚ ለማለፍ የሰው ሀይወት በጣም ውድ ነው። ለሁሉም ለሚሆነው ነገር ሁሉ ትርጉም ይኖረዋል። ይህ አመለካከትና በቅፅበት መሞቱ ለኛ ለምንወደው ለሀዘናችን ማፅናኛና ብሩህ የሆነ የሱ ትዝታ እንዲኖረን ይረዳናል።

በግብፅ በፖርት ሰይድ በአንድ ካፌ ቁጭ ብዬ ወደ ሀገሬ የሚወስደኝን ኮምፒየኝ የተባለ ጀልባ ስጠብቅ አንድ ሰው በአማርኛ ሲያናግረኝ ሰማሁ። ጀልባው እንደነዳጅ ሀይል የሚጠቀምበትን የድንጋይ ከሰል እየሞላ ነበር። በአማርኛ ያናገረኝ ሰው የንጉሡ ሾፌር መሆኑን ሳውቅ በጣም ነው የተገረምኩት።

የተላከው ከእቴጌዋ ነው። እቴጌዋ ከእየሩሳሌም ተመልሰው ወደ ኢንግላንድ እየሄዱ ነበር። በሚገርም ሁኔታ የኔን መምጣት ሰምተዋል እና መንገዴን እንዴት ብየ እንደምቀጥል ማወቅ ይፈልጋሉ። እኔም በምሄድበት ጀልባ ስለሚሄዱ ጀልባው ውስጥ መገናኘት የምንችል ከሆነ ብለው ጠይቀዋል።

በተከተሉት አምስት ቀናት ከእቴጌዋ ጋራ በየቀኑ እንገናኝ ነበር። በጣም የወዳጅነት ስሜት ያሳያሉ በርግጥም አቢሲኒያ ውስጥ ስላለው ሁኔታ ደግሞ ማወቅ ይፈልጋሉ። ከብደት ከመቀነሳቸውና ከሚታይባቸው የሀዘን ስሜት በመነሳት በቅርቡ ያሳለፉት ወራት ከባድ እንደሆነባቸው ያስታውቃል።



# ምዕራፍ ሀያ አምስት

## የውድቀቱ መንስኤዎች

የአቢሲኒያዋ አዲስ አበባ ለአቷ እየተቃረበ ነበር። በአለም ውስጥ የመጨረሻዋ የፊውዳልና ያልሠለጠነው ሀገር ዋና ከተማ ውስጥ ቅጥ ያጣ የውጭ ሰዎች ጥላቻ እንደ ድንገተኛ ጎርፍ ይገነፍል ነበር። በያሉበት ሆነው የውጭ ሰዎች ጣልያኖች ላይ ርግማንና ጥላቻ ያወርዱ ነበር በጎን ደግሞ በሽብር ተውጠው ጣልያኖቹ መጥተው እነዚህ ራሳቸው ያስታጠቋቸው የአቢሲኒያ ሰዎች ካደረጉባቸው ከበባ እንዲያድኗቸው ይፈልጋሉ።

በመስከረም ሀያ ሰባት የኢጣልያው መሪ ሙሶሎኒ በሚያዝያ ሀያ ሰባት ለመላው የኢጣልያ ህዝብ አዋጅ እንዲነገር ትዕዛዝ ሠጥቷል። ለላላ ሚሊዮን የሚሆኑት ጥሪው የተደረገላቸው ጣልያኖች የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አዳምጠዋል።

> "የአብዮቱ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች፤ መላው የኢጣልያ ወንዶችና ሴቶች፤ ከተራሮችና ከውቅያኖስ አድማስ የምትገኙ ኢጣልያውያንና የኢጣልያ ወዳጆች። ሰሙ። ማርሻል ባዶሊዮ የሚከተለውን የቴሌግራም መልክት አስተላልፎልኛል።
>
> 'ሚያዝያ 27 በአስር ሰአት እኔ በድል አድራጊው የኢጣልያ ሠራዊት ግንባር በመሆን አዲስ አበባ ገብቻለሁ'
>
> ለኢጣልያ ህዝብና ለመላው አለም ጦርነቱ እንደላቀለት አስታውቃለሁ። ለኢጣልያ ህዝብና ለመላው አለም ሰላም እንደተመለረተ አስታውቃለሁ። አቢሲኒያ ኢጣልያ ነች። ብዛት ያላቸው የቀድሞው የይሁዳ አንበሳ ሰርወ መንግስት ጎሳዎች በኢጣልያ ሶስት ቀለም ባንዴራ ስር በሰላም ለመኖርና ለመሥራት ፍላጎታቸውን በግልፅ አሳይተዋል። ያለቀላቸውና በሽሽት ላይ ያሉት

ባለባቶችና ራሶች ከዚህ በኋላ ምንም ሥልጣን የላቸውም:: ወደ ቦታቸው የሚመልሳቸው ምንም አይነት ህይል በአለም ውስጥ የለም::"

የሺ አመታት ዕድሜ ያለው ሀገርና መንግስት በፍጥነት ሊወድቅበት የቻለበት ምክንያት ምንድነው? ባለው የተራሮች አቀማመጥ፤ በተዋጊ ሰዎቹ ምክንያት እስከዛሬ ድረስ ከውጭ ከሚመጣ ጥቃት የተጠበቀ የሚመስል በተጨማሪም እስካሁን ድረስ ከውጭ ወራሪ ነፃነቱን ጠብቀ የኖረ አገር እንዴት በዚህ ባጭር ጊዜ በሰባት ወራት ውስጥ ይሸነፋል? ጀኔራል ስታራቼ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮቹ ፊት ለፊት በመሆን እና ከአንድ ሜጀር ጋር በድምሩ ከአንድ ሺ አምስት መቶ ወታደሮች ጋራ አንድ ጥይት እንኳን ሳይተኮስባቸው ገና የንጉሡ ጦር ሳይሸነፍ ሁለቱም ከተለያዩ አቅጣጫ የአቢሲኒያ ጥንታዊ ከተማ የሆነችው ጎንደር እንዴት ይገባሉ? ማንስ ነው ይህንን ማስረዳት የሚችለው? ወይም ደግሞ ማርሻል ባዶሊዮ እንዴት አድርጎ ነው በመንገዱ ላይ መዋጋት የሚችሉ በአስር ሺ የሚቆጠሩ የአቢሲኒያ ወታደሮች በየጫካውና በየቁጥቋጦው ተደብቀው ምንም ተቃዋሚ ሳያጋጥመው ከአሸንጌ ሀይቅ ተነስቶ አዲስ አበባ የገባው?

ለዚህ ውድቀት መንስኤ መልሱ ጠላት ለረዥም አመት በጥንቃቄ መደራጀቱ ወይም በአደረጃጀትና በጦር መሳሪያ የባለይነት ስለነበረው ብቻ አይደለም:: ለምክንያቱ ደግሞ የአቢሲኒያ ውስጣዊ ሁኔታ በተጨማሪ መመርመር አለበት::

ታላቋ ኢጣልያ የቅኝ ግዛቶቹዋ እንጀራ እናት እንደሆነች አድርጋ ነው የምትቆጥረው:: ድሃና በህዝብ ብዛት የተወጠረችው ኢጣልያ ከቁጥር በላይ ላደገው ህዝቧና ለምታመርተው ቁሳቁስ ገበያ ቅኝ ግዛት በጣም ያስፈልጋት ነበር:: አቢሲኒያ እስከአሁን ድረስ በቅኝ ገዥዎች ሳትወረር የቆየች አገር ባላት የተፈጥሮ ሀብት የተነሳ ምክንያት ኖረም አልኖረም ኢላማ ትሆናለች:: በድክመት የታቀደ ጥቃት በ1888 በአድዋ ተሞክሮ ከሽፏል:: የሚቀጥለው ጥቃት በደንብ የታቀደና የተዘጋጀ መሆን ነበረበት:: በአድዋ የደረሰው ሀፍረት መታጠብ ነበረበት::

ሰለዚህ ለአርባ አመት በሙሉ ጉልበት የተጠናከረና በደንብ የተደራጀ ዝግጅት ተጀመረ:: ጣልያኖች በመላው አቢሲኒያ የተሠራጩ የንግድ ወኪሎች መሰረቱ:: በወኪሉ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሰላይ፤ ሀኪምና የቴሌግራም ሠራተኛ ይጨምራል:: የወኪሉ ዋና አላማ ከሰዎች ጋር ግንኙነት መመስረት፤



አሰተሳሰባቸውን መማር፤ ለወደፊት የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፤ ኢጣልያን ተወዳጅ ለማድረግ ስጦታ በአልኮሆል፤ የሚያብረቀርቁ የታደሱ የድሮ ጠመንጃዎችንና ገንዘብም በመስጠት ነበር:: ሀኪሙ የታመሙ ድሆችን የነፃ ህክምና መስጠትም ከላይ ከተጠቀሰው ግብ ጋራ አብሮ የሚሄድ ነበር:: ቴሌግራም ሠራተኛው በተራው የታየውንና ውጤታማ የሆኑ ሥራዎችን ሪፖረት መላክ ነበረ ሥራው::

ለሰላማዊ ሥራ ነው ተብሎ አቢሲኒያ ውስጥ የሰዎች ቡድን በዚህ በዚያም ይላኩ ነበር:: ነገር ግን ዋናው አላማቸው በጣም ጠቃሚ የሆኑ የአገሪቱን ቦታዎች ማወቅና ካርታ ማንሳት ነበር::

ይህ በሙሉ ጉልበት የተደረገው የአቢሲኒያ ጥናት ውጤታማ ነበር ምክንያቱም ስለአበ.ሲኒያ በጣም አዋቂ ኤክስፐርቶች ኢጣልያውያን ነበሩ እንደ ባሮን ፍራንቸቲ እንደ ፖላራ እንደ ታላሞንቲ ና ደ ካስትሮ የመሳሰሉት ሰዎችና ሌሎችን ጨምሮ::

በተከተሉት አመታት ኤርትራና ሶማሊ በቁጥጥራቸው ስር ሆኑ ለከባድ ወይም ብዛት ላለው መጓጓዣ የሚሆኑ መንገዶች ተሠሩ::

“ኢጣልያ ያገገመ በሽተኛ ነች” የአንድ ዲፕሎማት ንግግር ነበር በአዲስ አበባ:: በካፖሬቶ ጊዜ የነበሩ ጣልያኖቹ አሁን ካሉት ጋራ ተመሳሳይ አይደሉም:: የአለም ጦርነት ትምህርት ሰጥቷቸዋል የቀረውን ደግሞ ከሙሶሎኒ ተምረዋል::

የቅኝ ግዛት ጦርነት በዚህ በጣም በተደራጀ ሁኔታ ተዘጋጅቶ አያውቅም:: ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል:: በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የኢጣልያ ወታደሮች መርከብ ላይ መውጣት ብቻ ነው ከዚያም ከኔፐልስና ከጀኖአ ተነስቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ደጋማው የኤርትራ ቦታዎች ድንኳንና አልጋ ተዘጋጅቶ የበሰለ ምግብ ወደ ሚጠብቃቸው ቦታ መውረድ ነው:: ከጠመንጃና ከሁለት መቶ ጥይቶች በስተቀር ወታደሮቹ ሌላ ሸክም እንዳይዙ ተደርጓል:: ሁሉም የሚያስፈልጋቸው ነገር በጭነት መኪና ይከተላቸዋል:: የጎደለ ነገር የለም:: በተቃራኒው ሁሉም ነገር ከሚገባው በላይ ነበር በተለይ በጦርነቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ:: በዚህ ግዙፍ በሆነ ድርጅት ምንም አይነት ስህተት አልነበረም::

ምናልባትም በነሐሴና በመስከረም ወራቶች ከምፅዋ ወደብ በስተቀር:: ለዚህ ትንሽ ወደብ ከመጠን በላይ ነው የሆነበት:: በቀን ወደ ዘጠና መርከቦች ከጫኑት የጦር መሳሪያ ጋር የወደቡን አቃ ማራገፊያ ያጣብቡ ነበር:: በዚህ

ጊዜ የሚፈለገውን ነገር በቀላሉ ማግኘት ወይም በሰርአት መጠበቅ አሰቸጋሪ ነበር፡፡ ጣልያኖቹ እራሳቸው አቢሲኒያ በዚያን ጊዜ ጥቂት ቦምቦች መጣል ብትችል ጥቂት ጀልባዎች ማሰመጥ ብትችል ወደቡ ጠቅላላውን ዝግትግት ብሎ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ያልቅ ነበር ይሉ ነበር፡፡

ነገር ግን የአየር ሀይሉ የኢጣልያ ግንባር ቀደምና ውጤታማ መሳሪያ ነበር፡፡ ለዚህ ምንም ጥርጣሬ የለም፡፡ በአየር ላይ የሚወርደውን ቦምብ ነበረ አቢሲኒያኖች በጣም የሚፈሩት፡፡ ጆሮ የሚበጥሰው ድምፅና የቦምብ ፍንጣሪው ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ነገር አይተው ለማያውቁ ሰዎች አሸባሪ የሆነ የሚያሰፈራ ሰሜት ነው የፈጠረባቸው፡፡ ምንም አይነት መከላከያ መንገድ ባለመኖሩ ሽብሩ ደግሞ በዛው ልክ ይጨምራል፡፡

በርግጥም የሠራዊቱ ወኔና ሰሜት በዚህ መንገድ እንዲሰበር ሆኗል ለነገሩ በዝግታ ቢሆንም፡፡ መሀል አገር ያለ ሰው እንኳን ማምለጥ የማይችልበት ሁኔታ ውሰጥ እንደሆነ አድርጎ ነበር የሚሰማው፡፡ በድንገት አውሮፕላን ይመጣና በጥቂት ደቂቃዎች ውሰጥ ቤቱ በሳት ይጋያል ሴቶችና ልጆች ይሞታሉ ወይም ይቆሰላሉ፡፡ እነዚህን ጭራቆች መከላከያ የለም፡፡ ታዲያ ሰዎች ዘመድና ልጆች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ወደ ጦር ሜዳ በመሄድ የጠላትን እንቅሰቃሴ መግታት ካልቻሉ መታገሉ ጥቅሙ ምንድን ነው? ሰለዚህ የልጆቻቸውንና የሚሰቶቻቸውን ህይወት ለማዳን ንብረታቸውንም ለመጠበቅ እቅም ከሌለው ንጉሥ ሰር ከመሆን በጉልበቱ ለላቀው ሀይል እጃቸውን ሰጡ፡፡

ጣሊያኖቹ ሰላይ አውሮፕላኖቻቸውንም በደንብ ነበር የተጠቀሙባቸው፡፡ የአቢሲኒያችን ካምፕ በማግኘት የወታደሩን ቁጥር መገመትና የጉዞ አቅጣጫውን ማወቅ ይችሉ ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ ጣልያኖቹ አብራሪዎቻቸው የጀግንነት ሥራ ሰሩ ብሉ ጉራ ለመንዛት በቂ ምክንያት የላቸውም፡፡ እንዴት ነው በአየር ላይ የሚቃወማቸው አንድ ጠላት እንኳን ሳይኖር ሰለ ጀግንነት የሚወራው? ፓይለቶቻቸው ልምድ የሌላቸው ለመሆኑ ኢላማቸውን የሚሰቱት ቦምቦች ወይም ያለምንም ሰሌት ዝምብለው የሚጣሉት ቦምቦች ምሰከር ናቸው፡፡

አንድ ጊዜ ዳባት ውሰጥ ቆሞ የነበረ የአቢሲኒያ አውሮፕላን በሁለት የኢጣልያ ቦምብ ጣዮች ይታያል፡፡ ከአጭር ከፍታ ሆነው ሰላሳ ቦምቦች ቢጥሉም ይሰቱታል፡፡ ከዚያ ወደ ምድር ዝቅ ብለው ያን ምሰኪን የፈረንሳይ ፖቴዝ አውሮፕላን አውቶማቲክ መሳረያ ያረበርቡበታል፡፡ ያ አልሰራ ሲላቸው የእሳት ቦምብ በመጣል በመጨረሻ በእሳት ሊያነዱት ችለዋል፡፡



የመርዝ ጋዝ በጣም ወሳኝ በሆነ ጊዜ እንደ መጨረሻ አማራጭ አድረገው ነበር ጣልያኖቹ የሚጠቀሙት፡፡ እዝነው ሳይሆን የመርዝ ጋዝ ውድ ሰለሆነ በነዚህ ያልሠለጠኑ ሰዎች ላይ በከንቱ እንዳይባከን ነው፡፡ ምናልባትም ለተሻለ አጋጣሚ በአውሮፓ ለሚደረግ ውጊያ እየቆጠቡ ነበር፡፡ አቢሲኒያውያን ደግሞ በአዲስ አበባ ገና አሰቀድሞ ጋዝ ሰለተባለ ነገር ትልቅ ፍራቻ ነበራቸው በተለይም አንድ የአዎሮፓ የጥርሰ ህኪም ሰለ ጋዝ ፅሁፍ ከፃፈች በኋላ "ጋዝ" የሚለው ቃል ብቻ ሲጠራ ያንቀጠቅጣቸው ነበር፡፡

ጣልያኖቹ ደግሞ በአውሮፕላን በመላው አገሪቱ ወረቀት በትነዋል፡፡ በወረቀቱም የሚታወቁ የጋዝ አይነቶቸ፤ በውሰጣቸው ሰለሚገኙ ኬሚካሎች አሰቃቂ የሆነ ውጤታቸውና አንድ ሰው ደግሞ የጋዝ ማሰክ በማድረግ ብቻ ራሱን መጠበቅ እንደሚችል የሚገልፁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ለእያንዳንዱ አይነት ጋዝ በፅሁፉ ውሰጥ የመጨረሻው ቃል የሚለው ለነዚህ ጋዞች የተጋለጠ ሰው ምንም አይነት የመዳን ተሰፋ የለውም ነው፡፡

እነዚህ በራሪ ወረቀቶችም ደጃዝማች እያሴው ባሉበት ግንበር መጥተው ነበር በዚያን ጊዜም ለመርዙ መፈወሻ የመሆኑ እምሰት ሳጥን ሙሉ የሎሳንቲን መድሃኒት የመጣልን ጊዜ ነበር፡፡

በወረቀቱ ውሰጥ የተፃፈውን ነገር ወታደሮቹ ማወቅ ሲጀምሩ የነበራቸው ወኔ ሚሸሸ፡፡ በግልፅ ምንም አይነት ጋዙን የሚቋቋም ነገር አለመኖሩን የተረዱት፡፡ በጣም የተናደዱት ደጃዝማች ፅሁፉን የፃፈው ሰው መሰቀል አለበት አሉ እንደላቸው አባባል የአማርኛው ፅሁፍ እንኳን ራሱ አሰቀያሚ ነው የነበረው፡፡

ሰለ ፕሮፖጋንዳ ጥቂት ቃላት ለመጨመር፡፡ ጣልያኖቹ የአቢሲኒያውያን ሰነልቦናና አሰተሳሰብ አሰቀድመው በደንብ አጥንተውታል እና እንዴት አድርገው እንደሚያዳከሙትም ያውቃሉ፡፡ በጦርነቱ ጊዜ ፓምፍሌት ወይም በራሪ ወረቀቶችን በየጊዜው ይበትኑ ነበር ሁልጊዜም በመሀል አገር ስለ ጦሩና ሰለ ሕዝቡ ትክክለኛ ጊዜና ቦታ ጠብቀው ነበር የሚያደርጉት፡፡

ጦርነቱ በተጀመረበት ሳምንት ውሰጥ አቢሲኒያውያን የሚከተለው ወሬ ደርሷቸው ነበር፡፡

በሀገራችሁ የሚኖር ባህታዊ ከአመት በፊት የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮ ነበር "በ1928 በዘመነ ዮሀንሰ ታላቋ ኢጣልያ የበለጠ ታላቅ ትሆናለች"

በአቢሲኒያ ዘመን አቆጣጠር አራት አመታት በተራ በተራ በአራቱ ወንጌላውያን ሰም ይጠራሉ፡፡ ማቲዎሰ ማርቆሰ ሉቃስ ዮሐንስ ተብለው፡፡

ጳጉሜ ስድስት ቀን የሚሆነው ሁልጊዜ በዘመነ ዮሐንስ ጊዜ ነው፡፡ ይህ የባይዛንቲን አቆጣጠር ነው 1928 አመት ምህረት በአውሮፓውያን 1936 ነው፡፡

ብዙ ሰዎች ይህን ትንቢት የማይረባ ትርጉም የሌለው ጨዋታ ነው የሚሉት ነገር ግን አቢሲኒያውያን በባህታዊያን ያላቸውን ሙሉ እምነት ለተረዳ ሰው ጣልያኖች አቢሲኒያኖችን በደንብ አድረገው እንደሚያውቁ መገንዘብ ይችላል

አንግዲህ ጣልያኖች የአቢሲኒያውያንን ወኔ ለመስበር የተጠቀሙባቸው እነዚህ ሁሉ ዘዴዎች ለአቢሲኒያ በፍጥነት መወድቅ በቂ ምክንያት ናቸው ካልተባሉ ታዲያ ትክክለኛው አገሪቱን ለውድቀት የዳረጋት በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ምን ነበር?

## 1. በራስ መተማመንና ስንፍና

የአቢሲኒያ የራሳቸው ታሪክ ፀሀፊዎች ህዝቡን ከጥንት ጀምሮ ነፃ የሆነች አገር ነች እያሉ ሲነግሩ ነበር፡፡ ከነጮች ጋራ በተደረገው አንድ ጦርነት በ1896 (እኤአ) አስደናቂ ድል ተጎናፅፈዋል፡፡ እንግሊዝና ፈረንሳይ መሬታቸውን አንደሚመኙ ግን ደፍረው እንዳላጠቁ ያውቃሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአለም ውስጥ ጥሩ ተዋጊዎች እንደሆኑና የማይሸነፉ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ አድርጎአቸዋል፡፡ ከአቢሲኒያውያን ጋራ ጥቂት ጊዜ ያሳለፈ ሰው አቢሲኒያውያን ኩሩና በራሳቸው የሚተማመኑ መሆናቸውን ማወቅ ይችላል፡፡

የዚህ ውጤት ደ'ግሞ ስንፍና ነበር ለረዥም ጊዜ ሥር የሰደደም ነበር፡፡ ማን ነው የሚያጠቃቸው? እንደዛ ከሆነ ደግሞ አገርን ለመከላከል ምን አስጨነቃቸው ወይም በአውሮፓውያን ሞዴል ሠራዊት መገንባት ለምን ያሰፈልጋል? እያንዳንዱ አቢሲኒያዊ ከትውልዱ ተዋጊ ነው ጠመንጃውንም ሆነ ጎራዴውን ያለምንም ችግር በደንብ መጠቀም ያውቅበታል፡፡ ሥልጠና? ያ ምን ጥቅም አለው በተለይ ጣልያኖች በሰአታት ወስጥ ከፍተኛ ሽንፈት ሲደርስባቸው ካዩ በኋላ ?

የነበራቸው በራስ መተማመን ስሜት ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል በተለይም ለአመታት ወደ ሀገሪቱ በሚመጡት አውሮፓውያን ሽንገላና አስመሳይ ሙገሳ በየጊዜው ሲደርግላቸውም ስለነበር፡፡



ይህንን አደጋ በደንብ ተረድተው የነበሩት የመጨረሻው ንጉሥ ነበሩ፡፡ ሠዎቻቸውን ለማስረዳትና ለማስገንዘብ እና የነበረውን ሁኔታም ለማሻሻል ሞክረው ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ብቸኛ በሰውነት ደቀቅ ያለ ሰው ከአሥራ አምስት ሚሊዮን ስንፍና የተሞላበት አንጎል ጋራ ምን ፋይዳ ማምጣት ይችላል? ከዚህ በላይ ንጉሡ ዘግይተው ነው የደረሱት፡፡ ወደኋላ በታዩት አመታት ሙከራቸው በሙሉ ተስፋ አስቆራጭ ነው የሚል ደረጃ እንደደረሱ ያስታውቅ ነበር፡፡ ከአቅማቸው በላይ ነበር፡፡ ለማሻሻል የነበራቸውን ብርቱ ምኞትና ፍላጎት አጡ፡፡

## 2. የውስጥ እርስ በርስ ባላንጣነትና ደስተኛ አለመሆን

ሌላ ሰው ደስ የሚለውን መናገር ይችላል ነገር ግን አፄው በዚያን ጊዜ ተወዳጅ አልነበሩም፡፡ ለአብዛኛው ህዝብ የህገሪቱ መሥራች የሆኑትን የሚኒሊክን ዙፋን በጉልበቱ የወሰደ ሰው ነበሩ፡፡ የኦሮሞ ተወላጆች በሙሉ እፄ ምኒሊክ በነሱ ላይ የሾሟቸውን ልጅ ኢያሱን አልረሱም፡፡

በየአመቱ ግብር እየተጨመረ በገበሬዎች በኩል መማረርን አስከተለ፡፡ እንደ አውነቱ ከሆነ ንጉሡ የተለያዩ ግብሮች እንዲቆሙ ትዛዝ ቢሰጡም በየአቅራቢያው በሚገኙ ሹማምንቶች ትዛዙ ተቀባይነት ስላልነበረው በአጅ እዙር ደካማ ማእከላዊ መንግስት ሆኖ በመታየቱ የመከፋትን ስሜት ፈጠረ፡፡ በአካባቢ ገዥዎች መሀከል የባላንጣ ስሜት በየጊዜውና አሁንም ድረስ በአቢሲኒያ ይታያል፡፡ ከንጉሡ ፊት አንዱ ሌላውን ይኮንናል፡፡ ሰው ሆኖ መሳሳት ያለ ነገር ነው ንጉሡም ደጋግመው በስህተት ትክክለኛውን ወገን አልያዙም፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ እሳቸው ሲያደርጉት እንደነበረው በሥራቸው ባሉ ሰዎች መሀከል በነበረው ጠብ ውስጥ ገብተው በችኮላ ውሳኔ ለአንዱ ወይ ለሌላው ወገን መስጠት አልነበረባቸውም፡፡ ጉዳዩን በውል ለመመርመር በቂ ጊዜ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ በአማካሪዎቻቸው አማካኝነት ወደ ተሳሳተ እቅጣጫ ይሄዱ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በየክልሉ ባሉ ሹማምንቶች ላይ የመከፋት ስሜትን ቀሰቀሰ፡፡

## 3. ንግርትና ቅስና

ንግርት ለኢትዮጵያ ውድቀት ምክንያቶች ከሆኑት አንዱ ነው ብሎ መናገር ትንሽ አንግዳ ነገር ይመስላል። ያለውን ተፅእኖ ከመጠን በላይ ሳያጋንኑ ግን ተፅዕኖ እንዳለው ማመን ተገቢ ነው። አቢሲኒያውያን በንግርት የሚያምኑ ሰዎች ናቸው። በጊዜው በመላው ሀገሪቱ የተሠራጩ ንግርት ተናጋሪዎች የሚሉትን በቀላሉ የሚቀበሉና የሚፈሩ ነበሩ። *ትንቢት ወይም ንግርት ተናገሪዎች ደግሞ የተለያዩ ነበሩ እንደ የኦሮሞ ቃልቻ፣ ሼኮች፤ ደብተራና ጠንቋዮችን ጨምሮ።

በቅርብ ጊዜ የተለያዩ ትንቢቶች በየጊዜው ይነገሩ ነበር ሁሉም ግን ተመሳሳይ አባባል ነበረባቸው።

"ከውቅያኖስ ማዶ በሚመጡ ሰዎች ትልቅ ጦርነት ይመጣል። ቁጥራቸው እንደ አንበጣ ብዙ ነው። በአፍንጫቸው እሳት የሚረጩ ክንፍ ያላቸው ፈረሶች ሀገሪቱን በመላ ይወሩና ይወስዷታል። ረሃብና በሽታም ይከተላል። የወራሪዎቹ ዙፋንም የመጡበት ጎዳናም ከፍት ይሆናል። ይህ ሁኔታ ግን ብዙም አይቆይም ቢበዛ ሶስት ወር ወይም ሶስት አመት ብቻ ነው። አዲስ ንጉሥ የእውነተኛው አምነት ጠባቂና ድሃን የሚወድ ወደ ዙፋኑ ይወጣል ምክንያቱም ከውቅያኖስ ማዶ የመጣው ሀይል በጎረቤቱ ይሸነፋል"

ጦርነቱ እንደተጀመረ በመሃል አገር የሚኖረው የአቢሲኒያ ሰው ጦርነቱን አቢሲኒያኖች ያሸንፋት ይሆን ብሎ ራሱን እየጠየቀ ነበር። መልሶ መላልሶ የሚሰማው ደግሞ "አዎ ግን ይኸኛው ወይም ሌላኛው ትንቢት ተናገሪ በዚህ መንገድ ወይም በሌላ መንገድ ነው ያለው"

ወደ ጦር ሜዳ ሄዶ ጠላትን ለመምታት በነበራቸው ፅኑ ፍላጎት ሠራዊቱ ንግርት ነጋሪዎቹ ያሉትን ነገር አላሰተባቃውም ነበር። ነገር ግን ጦርነቱ እየተራዘመ ሲሄድና በጦርነት መሸነፍ ሲመጣ ከሰሟቸው ንግርቶቹ ስለመጥፎዎቹ ማሰብ ጀመሩ።

---

*ትንቢት ተናጋሪዎችን በተመለከተ ገሪማ ታፈረ በመፅሐፋቸው (ጎንደሬ ቢጋሻው፣ ገፅ 5) በጊዜው በየአውራጃውና በየወረዳው የሚኖሩ ብለው የሃያ ሶስት ሰዎች ስም ዝረዝር አስቀምጠዋል። ስም ዝርዝሩ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮችን ይጨምራል። እንደ ገሪማ አዘጋገብ ትንቢት ተናጋሪዎች ደግሞ ጣሊያኖቹ ላይ ጉዳት ማስከተሉን ይገልፃሉ ይህም ትንቢቱ አርበኞችን ስለሚያበረታታ ነበር።



ከፍተኛ ስልጣን ያለው እያንዳንዱ ጦር አዛዥ ደግሞ ጦር ሜዳ ተከትሎት የሚሄድ ደብተራ፣ ሼኪ ወይም ቃልቻ ነበረው። እነዚህም በየጊዜው የሚጠየቁና ለምክር የሚፈለጉ ነበሩ። አንድ አዛዥ አዋቂ ሳያማክር ወይም ሳይጠይቅ ዘመቻ ወይም ጦርነት መጀመር አለዚያም ጠንከር ያለ እንቅስቃሴ አያደርግም ነበር። የደጃዝማች እያሌው ጓደኛ እንደመሆኔ ለዚህ ጉዳይ አብሬያቸው እሄድ ነበር። ትዛዝ ይሰጥና በመጨረሻው ደቂቃ ይሠረዛል። ለምን? ሲባል ዋናው አዋቂ ዲበኩሉ ይህ ሙከራ ውጤት የለውም ብሏል ነው መልሱ። ጉዞ እየተደረገ ድንገት መሀል ላይ ይቆማል ምክንያቱም ፊት ለፊት ከሚጓዙት አንዱ ወፍ መንገድ ላይ አይቷል። የተሠጠ ትዛዝ መልሶ ይሻራል ምክንያቱም የወፍ ጩኸት ወይም የኤሊ ድምፅ ተሰምቷል።

ቄሶችን በተመለከተ በማጠቃለል ንጉሡ ከጠዋቱም ቢሆን የነበራቸውን የደከመ በራስ መተማመን መልሶ አዳከሞታል ማለት ይቻላል። የሀገሪቱ መሪ ተሃድሶ ለማድረግ በነበራቸው ዕቅድ መሠረትና ተጀምሮም በነበረው ሥራ የቤተክርስቲያንን ሐይል ለመገደብ ሞከረው ነበር። በዚህ ምክንያት በቄሶቹ በኩል ተወዳጅነት አልነበራቸውም። ካቶሊክ ናቸው ወይም ፀረ ማርያም ናቸው እያሉ ሲጠሯቸው ነበር ሲከፋም አገሩን የከዳ ይሏቸውም ነበር።

## 4. ደካማ አደረጃጀት

ከዚህ ቀደም አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ለውድቀቱ አንደኛው ምክንያት በግልፅ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የነበረው የከፋ አደረጃጀት ነበር። እስከ መጨረሻው ሰአት ድረስ ይህ ለአንድ ሀገር ህልውና ወሳኝ የሆነ ሥራ ተረስቶና ተንቆ ነበር። ከወድቀቱ ከብዙ አመታት በፊት ሕዝቡን እየቦጠቦጡ በአውሮፓውያን መልከ የከብር ዘበኛ ጦር ያደራጁ ነበር። ይህ የሰልፍ ወታደር አዲስ አበባ ተቀምጦ መጠን የሌለው ገንዘብ የሚወጣበት ሲሆን በሌላ በኩል በመሓል አገርና በየዳር ድንበሩ የተሰማራው የመከላከያ ሠራዊት በጣም ተዳከሞ ነበር።

ጣልያኖቹ በድንበራቸው ላይ ምሽጎችን በየተራ ሲገነቡና ወደ አቢሲኒያ ድንበር ውስጥ እየገቡ አስርና ከዚያ በላይ ኪሎሜትር መሬት ሲወስዱ ኢትዮጵያኖቹ እጃቸውን አጣምረው የምፀት ሳቅ እየሳቁ

ይመለከቱ ነበር፡፡ ደንበራቸውን ለመከላከል ሀሳቡ አልነበራቸውም በመሀል አገርም ቢሆን የወታደር ካምፕ መመስረቱ አልታያቸውም፡፡ በመሀል አገር ወታደራዊ ካምፕ ቢኖር ደግሞ የአካባቢ ሹማምንቶችን ታዘዦች አድርጎ ሥርአትም ይፈጥር ነበር፡፡

የተሾሙ አማካሪዎች በየተራ ይሁን ጉዳይ ቢያነሱም ንጉሡም ሆነ ሚኒስትሮቹ ነጮች ላይ ባላቸው የተፈጥሮ ጥርጣሬ ምክንያት ምክሩን አልተቀበሉም፡፡ ምክር ሲሰጥ በደንብ ያዳምጣሉ ከተወያዩም በኋላ ምክሩ ጠቃሚ ነው የተለየ ነው ይላሉ አማካሪውንም ያመሰግናሉ እንዲህ አይነት ብልሃት እነሱ በጭራሽ እንደማያስቡትም ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ደስተኛና የረካው አማካሪ አግሩ ሲወጣ የተናገረውን ነገር ረስተውታል ወይም ልዩ ነው የተባለውን ምክሩን ተቀብለው ርምጃ ላለመውሰድ ይወስናሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፊት ለፊት ጮክ ብለው በማዛጋት አማካሪውን ያበሳጫሉ፡፡ ጦርነቱ በር ላይ ሲደርስ ብቻ ነው በቂ ጠመንጃ ጥይትና መድፍ እንደሌላቸው ያወቁት የአየር መከላከያ አለመኖሩንም ጨምሮ፡፡ ከዚያ በኋላ  በግራም በቀኝም ማግኘት የሚችሉት ነገር ካለ መደራደር ይጀምራሉ፡፡

የጀርመን የይሁዳዊና ኢትዮጵያዊ ዝርያ ያለበት የትንሽ መሣሪያዎች ሻጭ አውሮፓ ተልኮ ልምድ የሌለውን የጦር መሳሪያ እንዲገዛ ይሆናል፡፡ ወጤቱ ለአቢሲኒያውያን የሚያሳፍር ነበር፡፡

በጦርነቱ ጊዜ ዕቃ ማጓጓዣ ማደራጀት አስቸጋሪ ስለነበር ወታደሮቹ በየጦር ሜዳው ይራቡ ነበር፡፡ አዲስ አበባና ደሴ ግን ከተራው ኢትዮጵያዊ የተዋጣው ሥጦታ መካዝኖችን ያጣብብ ነበረ፡፡ ምንም አይነት የህክምና እርዳታ የሌላቸው ብዛት ስላላቸው የጦር ክፍሎችስ ምን ይባላል? ለሁሉም ነገር ከውጭ የሚመጣ የቀይ መስቀል አምቡላንስ ይጠብቁ ነበር፡፡ ራስ እምሩ ሀኪምና የህክምና ቁሳቁሶች እንዲላክላቸው ሲጠይቁ መንግስት የሰጠው መልስ በሱዳን በኩል የሚመጣ የእንግሊዝ አምቡላንስ መንገድ ላይ ነው የሚል ነበር፡፡ የተባለው አምቡላንስ ሰላልመጣ ራሳቸው ለአርባ ሺ  ሰዎች ሀኪም መሆን ነበረባቸው፡፡

ለእንዲህ አይነቱ አሳዛኝ ደካማ አደረጃጀት ከመጀመሪያው ንጉሡ ራሳቸው ሀላፊነት እንዳለባቸው ነው፡፡ ይህ በሙሉ የሳቸው ጥፋት



ነበር፡፡ ጉዳዩን አቅልለውታል ወይም ከሥራቸው ያሉ ሰዎችን ስለማያምኑ ሀላፊነት መውሰድ እንዲማሩ እንኳን አልፈቀዱላቸውም፡፡ በዙሪያቸው የተሰበሰቡ ባለሥልጣኖች ከጥቂቶቹ በስተቀር ስነፍና የማይፈይዱ ነበሩ፡፡ የንጉሡ ፍላጎት ምን እንደሆን ባይታወቅም ይህ ነገር ደግሞ የራሱ ችግር ነበረው፡፡ ለባለስልጣኖቹ ንጉሡ ራሳቸው የረሱት ነገር መሆኑን እንኳን እያወቁ በራሳቸው አነሳሽነት ጉዳዮችን መፈፀም አይታያቸውም፡፡ ለትንሹና ጥቃቅን ነገር በሙሉ ንጉሡን መጠየቅ ነበረባቸው፡፡

## 5. የአቢሲኒያ በፍጥነት መሸነፍ በሊግ አፍ ኔሽንስ መተማመናቸው ነው

አቢሲኒያ የሊግ አፍ ኔሽንስ አባልነት የፈለገቸው ከጎረቤቶቿ የሚደርስባትን ጥቃት ለመከላከል ነበር፡፡ ያ መከላከያቸው ነበር እናም ተማምነውበት ነበር፡፡ ምክንያቱም ለኢቢሲኒያኖች ይህን ያህል ወጭ የሚፈጅ ማህብር ሀያል ቢሆን ነው ብለው ያስቡ ነበር፡፡


ወራቶች እያለፉ ሲሄዱም መግለጫዎች ከአንድ ኮሚቴ በሌላው ኮሚቴ ቢሰጥም ውጤት አልባ በመሆኑ ለኢትዮጵያውያኑ ቆይቶ ግልፅ የሆነው ነገር ምንም አቅም የሌለው ድርጅትን እንደጠባቂ አድርገው መተማመናቸው ነው፡፡  ጥርጣሬ በተሰፋ መቁረጥ ተተካ ዘግይተውም ነው ከዚህ ከማያስተማምንና ብዙ ገንዘብ የሚጨርስ ድርጅት ጋራ ልክልክ ባይኖራቸው ራሳቸውን በተሻለ መንገድ መከላከል ይችሉ እንደነበር የተረዱት፡፡  ይህን ድርጅት ባያምኑት ኖሮና ህጉና ደንቡን ባይቀበሉ የራሳቸው የጦር መሳሪያዎች ራሳቸውን በሚመቻቸው መንገድ ይኖራቸው ነበር ስለዚህም ጣልያኖች ጥቃት ሳይጀምሩ ገና እየተደራጁ እያሉ ማጥቃትም ይችሉ ነበር፡፡ ጠላት ራሱ እንኳን ቢሆን ማለትም ጣልያኖች ራሳቸው አቢሲኒያውያን ማሸነፍ ስላለመቻላቸው የጥርጣሬ ሃሳብ ነበራቸው፡፡

ስለዚህ እንደአቢሲኒያኖች ግንዛቤ ዋናው የሽንፈታቸው ምክንያት ሊግ አፍ ኔሽንስ ነው፡፡

ፍፃሜ

## ስለ ፀሐፊው ዶክተር ሃራልድ ናየስተሮም

ከዶክተር ቶማስ ፒ ኮልማን ሰሰ ሀራልድ ናየስተሮም ከፃፉት የእንግሊዘኛ ግጥም የተዘጋጀ



ዶክተር ሀራልድ ናይስተሮም

ሀራልድ ናየሰተሮም በጥር ወር በ1898 (እኤአ) በኤርትራ ውስጥ በለሳ በሚባል ቦታ በጭቃ ቤት ውስጥ ነው የተወለደው፡፡ ወላጆቹ ካርል ናይሰተሮምና አግነስ ናየሰተሮም በዚህ ቦታ ለአሰራ አምስት አመታት ኖረዋል፡፡ ቦታው አርስ በርስ በሚዋጉ ጎሳዎች የተከበበ ስለነበር ሁልጊዜም ፍርሃት ነበረ፡፡

የጭቃ ቤታቸው አንድ ከፍል ብቻ ሲሆን ወለሉም ከጭቃ ነው የተሰራው፡፡ ግድግዳው በጭቃና በአበት የተሰቀሰቀ ነበር፡፡ ፈጣሪን ሲያገሰግሉ ሰሰወጡ ምንም ጊዜ ቢሆን ድሃ ነን ብሰው አስበው አያውቁም፡፡

ሃራልድ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስዊድን ሲሄድ የሀያ ሁለት አመት ወጣት ነበረ፡፡ እናትየዋ ወጣቱን ኮሌጅ መግቢያ ደረጃ አሰኪደርስ ቤት ውስጥ ነበር ያሰተማሩት፡፡ ሰህከምና ትምህርትም ወደ ቤይሩት ሄዶ የሜዲካል ዲግሪ ተቀበሰ፡፡ ከዚያም ሰተጨማሪ ሥልጠና ወደ ፈረንሳይ ከሄደ በኋላ የህከምና ፈቃዱን በኒዮርክ ስቴት ነበር ያገኘው፡፡ ወደ ስዊድን ሲሄድም ከወደፊት ባሰቤቱ ጋራ ተገናኘ፡፡ ከሳፍል ቫርመላንድ ነበር ሴትዮዋ የመጣቻው ከዚያ በኋላ በሶስት ጦርነቶች ጊዜ ችግርና መከራም አብረው አይተዋል፡፡



አብረው ሲኖሩም ሁለት ልጆች ወልደዋል የመጀመሪያው ልጅ ወንድ ጋነር ተከታይዋ ደግሞ ሴቷ ብርጊታ ነበረች፡፡ ጋነር አሥራ ዘጠኝ አመት ሲሞላው የትምህርት ቤት ፈተናውን ከጨረሰ በኋላ የባህር ሐይል ውስጥ ተሰልፎ ጎትላንደ በምትባል መርከብ ተመድቦ ነበር፡፡

ሀራልድ ወደ ኢትዮጵያ በሄደበት ጊዜ ባሳቤቱ ማርታ ሳፍል ስዊድን ውስጥ ነበረች፡፡ በዚያም እያለች የወንድ ልጃቸውን የጋነርን ሞት ትሰማሰች፡፡ በመርከቧ ላይ በመድፍ ውስጥ አርሳስ ሲያስገቡ ፈንድቶ ከጋነር ጋራ ሶስት ሰዎች በቅፅበት ሕይወታቸው አልፏል፡፡ ሀራልድ በኢትዮጵያውያን ባህል መሰረት ለሶስት ቀናት በሀዘን ተቀመጠ ከዚያ በኋላ ስለዚህ አሳዛኝ ቀን አንስቶም አያውቅም፡፡ ማርታ ደግሞ በስዊድን በራሷ መንገድ ነበር ሀዘኗን የገለፀችው በየአመቱ ከጋነር ፎቶ ፊት ሰፊት ሻማ ታበራም ነበር፡፡

በ1928 እኤአ ወደ ኢትዮጵያ ሲመሰስ የከብር ዘበኛ ሀኪም ሆነ፡፡ ከሰባት አመታት አገልግሎት በኋላ ጦርነት መጣ ችግርም ተከተሰ፡፡ ፋሺስቶቹ ምንም ርህራሄም አልነበራቸውም፡፡ ደሀዋ ኢትዮጵያም እንደዚህ አይነት ሰቃይ ደርሶባት አያውቅም፡፡ በጦርነቱ ጊዜ ሀኪሙ ሀራልድ ከዳኞች እያሌው ብሩ ጦር ጋር በመዝመት ብዙ ፈተና እንደደረሰበት መፅሀፉ ያስረዳል፡፡

በደብረ ታቦር ከተማ ሀራልድ ለጣልያኖች እጁን ከሰጠ በኋላ የኢጣልያው ሜጀር ለሃራልድ ደብዳቤ እንደተሳከሰት ይነግረዋል፡፡ ባሰቤቱ ማርታ ሀራልድ በሕይወት ይኖራል በሚል ተሰፋ በስዊድን በጣልያን ኤምባሲ በኩል ነበር የላከችው፡፡ ከዚያም ሜጀሩ በተጫማሪ ነገር ሀራልድን አስገረመው፡፡ ሜጀሩ ሮም ደውሎ ወደ ስውዲን ከተሳሰፈ በኋላ ሬድዮውን ሰሀራልድ በመሰጠት ያንተ ነው እንደፈሰግህ ተናገር ብሎ ከባለቤቱ ማርታ ጋር አገናኝቶታል፡፡ ሀራልድ በህይወቱ እንደዚህ ቀን ተደስቶ እንደማያውቅ ይናገር ነበር፡፡

ከጦርነቱ በኋላ ሰዊዲን እንደተመሰሰ በሰፔይን የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ፡፡ ሀራልድም በቀይ መስቀል ሥር ስፔይን ሄደ እንደገናም ጦርነት አየ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፊንላንድ በነበረው ጦርነትም ከስዊድን በቀይ መስቀል ስር እንዲሄድ ሆኗል፡፡

በ1940 በስዊድን የሀኪምነት የሙያ ፈቃድ ተቀበለ እስከ 1945 ድረስ በሰዊዲን የህከምና ሙያ ሲሰራ ቆየ፡፡ በ1945 ወደ ትውልድ ቦታው ተመሰሰና በአድዋ በመንግስት ሥራ ሲሰራ ቆየ በኋላም በ1952 እኤአ በሚሲዮን ስር የሚፈልገውን ሥራ ጀመረ፡፡ ለአሥራ ሁሰት አመታት በአሰላ ሆስፒታል ያገለገለ ሲሆን የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት የጤና ጥበቃ ቢሮ ሀላፊም ነበር፡፡

አሥራ ሁለት ቋንቋዎች የመናገር ችሎታው አለም አቀፍ ዝናን ነው ያተረፈለት:: አዋሳ ቤት ሰርቶ በዚያው ጡረታ ወጣ:: በኋላም በህመም ምክንያት ሴት ልጃቸው ቢርጊታ መጥታ ቤታቸውን ትተው ወደ ስዊድን ተመለሱ:: በ1974 በህዳር ወር ስዊድን ሲገቡ አየጠበቋቸው የነበሩ መቶ የሚሆኑ ሰዎች በመዝሙር ነበር የተቀበሏቸው::

የመጨረሻ ቀን ታህሳስ 18 1974 እኤአ ነበር:: ሕይወቱ ከማለፉ በፊት በቦታው የነበረ ጓደኛው የሰማው ቃል ነበረ:: ቃሉን እንደተናገረም አረፈ::

"አባከህ የዳዊት መዝሙር ቁጥር አንድ መቶ ሰላሳትን አንብብልኝ"



## አስተያየት

መፅሐፍ ከመተርጎም መፅሐፍ መድረስ ይቀላል:: በመጀመሪያ ይህን ጠቃሚ መፅሐፍ ለመተርጎም ጊዜያቸውን መሰዋዕት ያደረጉትን ማመስገን እወዳለሁ:: ከምርመር አንፃር መፅሐፉ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ:: እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ሰንወርሰው የቆየነው የሀገራችን ታሪክ ከገዢዎች አንፃር የተፃፈ እየሆነ ትክክለኛውን የህዝብ ተሳትፎ ማወቅ አልተቻለም ነበር:: ይህ መፅሐፍ ከዚህ አኳያ ብዙ ለታሪክ ጥናት የሚጠቅሙ ነጥቦችን አስተላልፎልናል:: ታሪካቸው እምብዛም ያልታወቀው ደጃዝማች አያሌው ከባዱን የጠላት ጦር ለመመከት የተጠቀሙባቸውን ስልቶች የሰው ነፍስ በከንቱ እንዳይጠፉ ያሳዩትን የአመራር ብቃት እንዲሁም ለተማረኩ የጠላት ወገኖች ያሳዩትን ደግነት አሳምሮ አቅርቦታል:: በጣልያኖች በኩል የነበረውን የጦር መሣሪያ ዓይነትና ብዛት፤ ጣልያኖች ለ40 አመታት በተለያየ መልክ ወደ ኢትዮጵያ ሠርገው በመግባት ህዝቡን ባህሉንና የሀገሪቱን መልክአ ምድር በማጥናት ምን ያህል እንደተዘጋጁ፤ የመርዝ በምብ ጥቅም ላይ ማዋላቸውንና የምዕራባውያንን "እስቃቂ ኢሰብአዊ ሥልጣኔ" በሰፊው ዘርዝረውታል:: በሌላ አንፃር የኢትዮጵያውያን ጀግንነት ለነፃነት የተከፈለውን የወገን ውድ ዋጋ፤ የአመራሩን ብቃት ማነስና ጦርነቱን ማቸነፍ ያልተቻለበትን ጉዳይ ከነምክንያቱ አቅርቧል:: ጥቂት ገፆች በያዘ መፅሐፍ ከዚህ ቀደም ያልተጠቀሱ አዳዲስ የታሪክ ነጥቦች ቀርበውበታል::

ፋንታሁን ጥሩነህ (ዋሽንግተን ዲሲ)

በሞት ጉዞ ከቅዱስ ጊዮርስ ጋር በሚል ርዕስ የተፃፈውን መፅሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉመው ለአንባብያን ላቀረቡት ለዶክተር ገበየሁ ተፈሪና ለአቶ ደሳለኝ አለሙ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አገልፃለሁ::

መፅሐፉን በጥሩ አማርኛ መተርጎም ብቻ ሳይሆን፤ በመፅሐፉ መቅድም ላይ የፃፏቸው መግለጫዎችና አስተያየቶች አስተዋይነትና ሐቀኛነት አለባቸው:: የመፅሐፉ ደራሲ ሐኪም ሐራልድ ናየስተሮም ከዳጃዝማች አያሌው ብሩ ጋር በመሆን ወደ ሽሬ ጦር ግንባር ሄዶ እንዳባጉናና ስለህለሐ ላይ በተደረገው ጦርነት በዐይኑ ያየውን በጆሮው የሰማውን በእጁ ዳሶ ሰላከማቸው ቁስለኞች በየቀኑና በሰአቱ መዝግቦ ባቆየው ማስታወሻ መሠረት

የተፃፈ ታሪክ ስለሆነ፤ ለምናነበው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለታሪክ ተመራማሪዎችም በጣም ጠቃሚ የሆነ የጥናት ምንጭ ሊሆን ይችላል።

ዝነኛው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ያሳዩት የጦር አመራር ስልትና ዘዴ አስቀድመው ያዘጋጁት ስንቅና፤ ተዋጊዎቻቸው ለአውሮፕላን በምብ እንዳይጋለጡ ያደረጉት ጥንቃቄ በጣም ሊያስመሰግናቸው ሊያስከብራቸው ይገባል።

የጦር አዋጊዎቻቸው ፊታውራሪ ሽፈራው፣ ፊታውራሪ ነጋሽና ሌሎችም ያሳዩት ጀግንነት ዕፁብ ድንቅ ነው። በዘመናዊ የጦር ስልት የሰለጠነ፤ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ፤ ብዛት ያለቸው ታንኮችና የወታደር መጓጓዣ፤ በምብ የሚጥሉ አውሮፕላኖች የነበረውን የጣልያን ወታደር የኢትዮጵያ አርበኞች በአልቢንና በምንሽር ግፋ ሲል በመትረየስ ተዋግተው እንዳባጉና ላይ እንዳሸነፉት ያነበበ ሁሉ አንገቱን ቀና ደረቱን ለጠጥ አድርጎ በኢትዮጵያውነቱ ሊኮራ ይገባዋል። በዚያን ጊዜ የተከሰተውን የአርበኞች ጀግንነት የሚገልፅ ፉከራ ሚከተለው ነው።

ትግራይ ላይ ገዳይ እንዳባጉና
የተለየ ለት ፈሪና ጀግና

ትግራይ ላይ ገዳይ ሰለህለሐ
ያ ሁሉ ጣልያን ሲጠማው ውሀ

ይህ መፅሐፍ ደጋግመው ቢያነቡት አይሰለችም። ያለፉት ወገኖቻችን ምን ያህል ጠንካራና አገር ወዳድ እንደነበሩ በግልፅ ያሳያል። በበላይ መሪዎች ሆነ በሕዝቡ በኩል ካለማወቅ የተነሳ ብዙ ድክመቶች እንደነበሩ መፅሐፉ ይጠቁማል።

ዶክተር ጥላሁን እንየው

ይህ መፅሀፍ የ1928ን የፋሺስት ኢጣሊያ ወረራና በሰሜን ምእራቡ ግንባር የተፈፀሙትን ድርጊቶች በወፍ በረር ስንሰማ የነበረውን የወረራውን አስከፊነትና ጭፍጨፋ ለማንም ባልወገነ መልኩ የሚተርክ ሲሆን የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት የአመራሩን ደካማ የውጊያ ዝግጅትና ያልተመጣጠነ ትጥቅ በሚገባ ይገልፃል፡፡ ደራሲው የውጭ ዜጋ ቢሆንም ባህላችንን በሚገባ ስለሚያውቅ የብዙ ወራትን ውጊያ፣ መከራና የእለት በእለት ድርጊት በማይሰለችና አጓጊ በሆነ መልኩ ይገልፃል፡፡ ተርጓሚዎችም ይህንን የማይረሳ ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብ በአማርኛ እንዲያነበው ባማረ መልኩ በመተርጎማቸው መፀሀፉን በቀላሉ ተነባቢ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

**ፋሲል ጊዮርጊስ**

መፅሐፍ ከመተርጎም መፅሐፍ መድረስ ይቀላል፡፡ በመጀመሪያ ይህን ጠቃሚ መፅሐፍ ለመተርጎም ጊዜያቸውን መስዋዕት ያደረጉትን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ ከምርምር አንፃር መፅሐፉ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ፡፡ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ስንወርሰው የቆየነው የሀገራችን ታሪክ ከገዢዎች አንፃር የተፃፈ እየሆነ ትክክለኛውን የህዝብ ተሳትፎ ማወቅ አልተቻለም ነበር፡፡ ይህ መፅሐፍ ከዚህ አኳያ ብዙ ለታሪክ ጥናት የሚጠቅሙ ነጥቦችን አስተላልፎልናል ...

**ፋንታሁን ጥሩነህ (ዋሽንግተን ዲሲ)**

መፅሐፉን በጥሩ አማርኛ መተርጎም ብቻ ሳይሆን በመፅሐፉ መቅድም ላይ የፃፏቸው መግለጫዎችና አስተያየቶች አስተዋይነትና ሐቀኝነት አለባቸው፡፡ ...

**ዶክተር ጥላሁን እንየው**

እውነተኛ ታሪክ፣ ሚዛናዊ ፅሁፍ፣ አገራቸውን ለመጠበቅ የዘመቱ ኢትዮጵያውያን የደረሰባቸውን መከራና ግፍ በስዕላዊ ሁኔታ የዘገበ ፅሁፍ፡፡ ሌሎችም ርዕሶች፣ ስለጥሬ ሥጋ አበላል አጀማመር፣ ስለ "እያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" ታሪካዊ ምክንያት፣ አስደናቂ የከምባታ ተወላጆች ጀብድና ሌሎችም፡፡ መፅሐፉን ማንበብ ጀምረው ማቆም ያልቻሉ ዕንቅልፍ አጥተው ማደራቸውን የመሰከሩለት ፅሁፍ፡፡



Chibo Light Book
www.chibolight.com
Info@chibolight.com

ISBN 978-0-692-26893-3 $20.00
52000>
9 780692 268933